## ውዳሴሃ ለእግዝዕትነ ማርያም ድንግል

## ወላዲተ አምላክ ዘይትነበብ በዕለተ ሰኑይ

፩. ፈቀደ እግዚእ ያግዕዞ ለአዳም ሕዙነ ወትኩዘ ልብ ወያግብኦ ሀበ ዘትካት መንበሩ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፪. ሰረቀ በሥጋ እምድንግል ዘእንበለ ዘርአ ብእሲ ወአድኃነነ ለሔዋን እንተ አስሃታ ከይሲ ፈትሃ ላዕሌሃ እግዚአብሄር እንዘ ይብል ብዙሃ አበዝሆ ለህማምኪ ወለጻዕርኪ ሠምረ ልቡ ኃበ ፍቅረ ሰብዕ ወአግአዛ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፫. ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ዘተሰብአ ወኃደረ ላዕሌነ ወርኢነ ስብሓቲሁ ከመ ስብሐተ አሐዱ ዋሕድ ለአቡሁ ሠምረ ይሣሃለነ ሰአሊ ለነ ቅድስት

፬.ርዕየ ኢሳይያስ ነቢይ በመንፈሰ ትንቢት ምስጢሮ ለአማኑኤል ወበእንተዝ ጸርሃ እንዘ ይብል ሕጻን ተወልደ ለነ ወልድ ተውህበ ለነ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፭.ተፈሣሕ ወተኀሰይ ኦ ዘመደ እጓለ እመሕያው እስመ አፍቀሮ እግዚአብሄር ለዓለም ወመጠወ ወልዶ ዋሕደ ከመ ይሕየው ኩሉ ዘየዓምን ቦቱ እስከ ለዓለም ፈነወ ለነ መዝራዕቶ ልዑለ ሰአሊ ለነ ቅድስት

፮. ዘሀሎወይሄሉ ዘመፅዓ ወካዕበ ይመፅዕ ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ዘተሰብዓ ዘእንበለ ውላጤ ኮነ ፍጹመ ሰብአ ኢተበአደ ወኢተፈ ልጠ በኩሉ ግብሩ ወልድ ዋሕድ አላ አሐዱ ራእይ ወአሐዱ ህላዌ ወአሐዱ መለኮት ዘእግዚአብሄር ቃል። ሰ.ለ.ቅ

፯. ተፈሥሒ ኦ ቤተልሔም ሀገሮሙ ለነቢያት እስመ በኀቤኪ ተወልደ ክርስቶስዳግማይ አዳም ከመ ያግብዖ ለአዳም ቀዳሚ ብእሲ እምድር ውስተ ገነት ይስአር ፍትሐሞት ኦ አዳም መሬት አንተ ወትገብዕ ውስተ መሬት ኀበ ሀለወት ብዝሕት ኃጢአት በህየ ትበዝህ ጸጋ እግዚአብሄር። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፰.ትትፌሣሕወትትኃሠይ ኩሉ ነፍስተ ሰብእ ምስለ መላእክት ይሴብሕዎ ለክርስቶስንጉሥ ይጸርሁ ወይብሉ ስብሐት ለእግ ዚአብሄር በሰማያት ወሰላም በምድር ስምረቱ ለሰብእ እስመ ሠዐረ ዘትካት ወነሰተ ምክሮ ለጸላኢ ወሰጠጠ መጽሐፈ እዳ ሆሙ ለአዳም ወለሔዋን ወረሰዮሙ አግዐዝያነ ዘተወልደ ለነ በሀገረ ዳዊት መድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፱.ብርሃንዘ በአማን ዘያበርህ ለኩሉ ሰብእ ለእለ ይነብሩ ውስተ ዓለም በእንተ ፍቅረ ሰብእ መጻእከ ውስተ ዓለም ወኩሉ ፍጥረት ተፈሥሐ በምጽአትከ እስመ አድኀንኮ ለአዳም እምስህተት ወረሰይካ ለሔዋን አግዐዚተ እምጻ እረ ሞት ወወሀብከነ መንፈሰ ልደት ባረክናከ ምስለ መላእክቲከ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

## ሶርያዊው ቅዱስ ኤፍሬም የደረሰው ሰኞ የሚጸለይ አምላክን የወለደች የድንግል ማርያም ምስጋና

1. ጌታ ልቡ ያዘነና የተከዘ አዳምን ነፃ ያወጣውና ወደ ቀድሞ ቦታው ይመልሰው ዘንድ ወደደ። ቅድስት ሆይ ለምኝልን.

2. ከድንግል ያለወንድ ዘር በሥጋ ተወለደና አዳነን ከይሲ (ዲያብሎስ) ያሳታት ሔዋንን እግዚአብሄር ምጥሽንና ጻዕርሽን አበዛዋለሁ ብሎ ፈረደባት ሰውን ወደደና ነፃ አደረጋት። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

3.ሰው የሆነና በእኛ ያደረ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ክብሩንም ለአባቱ አንድ እንደመሆኑ ክብር አየን። ይቅር ይለን ዘንድ ወደደ። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

4. ነቢዩ ኢሳይያስ በመንፈስ ቅዱስ የአማኑኤልን ምስጢር አየ ስለዚህም ሕጻን ተወለደልን ወልድም ተሰጠልን ብሎ አሰምቶ ተናገረ። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

5. ሰው ሆይ ፈጽመህ ደስ ይበልህ እግዚአብሄር ዓለሙን ወዶታልና አንድ ልጁንም የሚያምንበት ሁሉ እስከ ዘለዓ ለም ፈጽሞ ይድን ዘንድ አሳልፎ ሰጥቷልና ልዑል ክንዱን ሰደደልን። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

6. የነበረው የሚኖረው የመጣው ዳግመኛም የሚመጣው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ያለመለወጥ ፍጹም ሰው ሆነ። አንዱ ወልድ በስራው ሁሉ አልተለየም የእግዚአብሄር ቃል መለኮት አንድ ነው እንጂ ። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

7.የነቢያት ሀገራቸውቤተልሔም ሆይደስ ይበልሽ ሁለተኛው አዳም ክርስቶስ በአንቺ ዘንድ ተወልዷልና የቀድሞውን ሰው አዳምን ከምድር (ከሲኦል)ወደ ገነት ይመልሰው ዘንድ አዳም ሆይ መሬት ነበርክና ወደ መሬት ትመለሳለህ ብሎ የፈረደበት ንም የሞት ፍርድ ያጠፋለት ዘንድ።ብዙ ኃጢአት ባለችበት የእግዚአብሄር ጸጋ ትበዛለች። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

8.የሰው ሁሉ ሰውነት ደስ ይላታል።በሰማይ ለእግዚአብሄር ምስጋና ይሁን በምድርም ሰላም ለሰውም እርሱበሚፈቅደው እያሉ አሰምተው ንጉሥ ክርስቶስን ከመላእክት ጋር ያመሰግ ኑታል። የቀድሞውን እርግማን አጥፍቷልና የጠላትን ምክሩን አፈረሰበት።ለአዳምና ለሔዋን የእዳ ደብዳቤያቸውን ቀደደ ላቸው፤በዳዊት ሀገር የተወለደ መድኃኒታችንኢየሱስክርስቶስ አዳምንና ሔዋንን ነጻ አደረጋቸው። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

9. በዚህ ዓለም ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ የምታበራ እውነተኛ ብርሃን ስለ ሰው ፍቅር ወደ ዓለም የመጣህ ፍጥረት ሁሉ በመምጣትህ ደስ አለው አዳምን ከስህተት አድነኸዋልና ሔዋ ንንም ከሞት ጻዕረኝነት ነጻ አድርገኻታልና የምንወለድበትን መንፈስ (ረቂቁን ልደት)ሰጠኸንከመላእክትጋርም አመሰገንህ ቅድስት ሆይ ለምኝልን

## ውዳሴሃ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተአምላክ ዘይትነበብ በእለተ ሠሉስ

፩. አክሊለ ምክሕነ ወቀዳሚተ መድኃኒትነ ወመሠረተ ንጽሕነ ኮነ በማርያምድንግል እንተ ወለደት ለነ ዘእግዚአብሄር ቃለዘኮነ ሰብአ በእንተ መድኃኒትነ እምድኅረ ኮነ ሰብአ ጥዩቀ አምላክፍጹም ውእቱ ወበእንተዝ ወለደቶ እንዘ ድንግልይእቲ  መንክር ኃይለ ወሊዶታ ዘኢይትነገር። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፪.እስመ በፈቃዱ ወበሥምረተ አቡሁወመንፈስ ቅዱስ መጽአ ወአድኅነነ። ዐቢይ ውእቱ ስብሐተ ድንግልናኪ ኦ ማርያም ድንግል ፍጽምት ረከብኪ ሞገሰ እግዚአብሄር ምስሌኪ አንቲ ውእቱ ሰዋስው ዘርዕየ ያዕቆብእምድር ዘይበጽሕ እስከ ሰማይ ወመላእከተእግዚአብሄርየዐርጉ ወይወርዱ ውስቴታ።  ሰአሊ ለነ ቅድስት

፫.አንቲ ውእቱ ዕፅ ዘርዕየ ሙሴ በነደ እሳት ወኢትውዒ ዘውእቱ ወልደ እግዚአብሄር መጽአ ወኅደረ ውስተ ከርስኪ ወእሳተ መለኮቱ ኢያውዓየ ሥጋኪ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፬.አንቲ ውእቱ ገራኅት ዘኢተዘርአ ውስቴታ ዘርእ ወጽአ  እምኔኪ ፍሬ ሕይወት። አንቲ ውእቱ መዝገብ ዘተሣየጠ ዮሴፍ ወረከበ በውስቴታ ባሕርየ ዕንቈ ክቡረ ዘውእቱ መድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ተጸውረ በከርስኪ ወወለድኪዮ ውስተ ዓለም :: ሰአሊ ለነ ቅድስት

፭.ተፈሥሒ ኦ ወላዲተ እግዚእ ኃሴቶሙ ለመላእክት ተፈሥሒ ኦ ንጽሕት ዘናሆሙ ለነቢያት ተፈሥሒ እስመ ረከብኪ ሞገሰ እግዚአብሄር ምስሌኪ ተፈሥሒ እስመ ተወከፍኪ ቃሎ ለመል አክ ፍሥሐ ኵሉ ዓለም ተፈሥሒ ኦ ወላዲተ ፈጣሬ ኵሉ ዓለም። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፮.ተፈሥሒ እስመ ድልወ ተሰመይኪ ኦ ወላዲተ አምላክ ተፈ ስሒ ኦ መድኃኒታ ለሔዋን ተፈሥሒ እንተ አጥበውኪ ሐሊበ ለዘይሴስዮ ለኵሉ ፍጥረት ተፈሥሒ ኦ ቅድስት እሞሙ ለኵ ሎሙ ሕያዋን ናንቀዐዱ ኀቤኪ ትስአሊ በእንቲአነ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፯. ኦ ድንግል ኦ ቅድስት ኦ ወላዲተ እግዚእ እስመ ወለድኪ ለነ ንጉሠ መንክር ምሥጢር ኅደረ ላዕሌኪ ለመድኃኒተ ዚአነ ናርምም እስመ ኢንክል ፈጽሞ ጥንቁቀ ነጊረ በእንተ እበዩ ለውእቱ ገባሬ ሠናያት በብዙኅ መንክር ራዕይ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

## ማክሰኞ የሚጸለይ አምላክን የወለደች የድንግል ማርያም ምሥጋና ሁለተኛ ክፍል

1. የመመኪያችን ዘውድ የድኅነታችን መጀምሪያ የንጽሕናች ንም መሠረት  እኛን ስለማዳን ሰው የሆነ የእግዚአብሄርን ቃል በወለደችልን በድንግል ማርያም ተገኘልን።ሰው ከሆነ በኋላም ፍጹም አምላክ ነው ስለዚህም በድን ግልና ወለደችው ድንቅ የሆነ የመውለድዋ ችሎታ የማይመረመር/ሊነገር የማይቻል/ ነው። ቅድስት ሆይ ለምኚልን

2.በእርሱ ፈቃድ በአባቱ ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ መጥቶ አዳነን በድንግልና ፍጽምት የሆንሽ ማርያም ሆይ የድንግልናሽ ምስጋናና ክብር ታላቅ ነው።እግዚአብሄር ከአንቺ ጋር ቢሆን ባለሟልነትን አግኝተሻልና። ያዕቆብ ከምድር እስከ ሰማይ ደርሳየእግዚአብሄርመላእክት ሲወጡባትና ሲወርዱባት   ያያት መሰላል አንቺነሽ ። ቅድስት ሆይ ለምኚልን

3.ሙሴ በነደ እሳት ሳትቃጠል ያያት ዕፅ አንቺ ነሽ ይኸውም መጥቶ በማሕጸንሽ ያደረው የእግዚአብሄርልጅ ነው የመለኮቱ እሳትነት ሥጋሽን አላቃጠለውም። ቅድስት ሆይ ለምኚልን

4. ዘር ያልተዘራባት እርሻ አንቺ ነሽ የሕይወት ፍሬ ከአንቺ ወጣ ዮሴፍ የዋጃትና የከበረ እንቁን ያገኘባት ሣጥን አንቺ ነሽ ይኸውም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በማሕጸንሽ አደረ በዚህ ዓለምም ወለድሽው። ቅድስት ሆይ.ለምኚልን

5.የመላእክት ደስታቸው የሆነ ጌታን የወለድሽ ሆይ ደስ ይበልሽ የነቢያት ዜናቸው ንጽሕት ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚ አብሄር ከአንቺ ጋር ቢሆን ባለሟልነትን አግኝተሻልና ደስ ይበልሽ የዓለም(የሰው)ሁሉ ደስታ የሆነ የመልአኩን ቃል ተቀብለሻልና ደስ ይበልሽ። ዓለምን ሁሉ የፈጠረ ጌታን የወ ለድሽ ሆይ ደስ ይበልሽ። ቅድስት ሆይለምኚልን

6.በሚገባ የአምላክ እናት ተብለሻልና ደስ ይበልሽ የሔዋን መድኃኒትዋ ሆይ ደስ ይበልሽ ፍጥረቱን ሁሉ የሚመግበ ውን እሱን ጡትሽን አጥብተሽዋልና ደስ ይበልሽ የሕያዋን (የጻድቃን)ሁሉ እናታቸው ቅድስት ሆይ ደስ ይበልሽ ። ትለምኚልን ዘንድ ወደ አንቺ እናንጋጥጣለን። ቅድስት ሆይ ለምኚልን

7.ድንግል ሆይ ቅድስት ሆይ ጌታን የወለድሽ ሆይ እኛን ለማዳን ድንቅ ምሥጢር/ተዋሕዶ/በአንቺ ቢደረግ ንጉሥን ወልደሽልናልና ፍጥረታትን በልዩ ልዩ መልክ የፈጠረ የእር ሱን የገናንነቱን ነገር ፈጽመን መናገር አይቻለንምና ዝም እንበል። ቅድስት ሆይ ለምኚልን

፰. ቃለ አብ ሕያው ዘወረደ ውስተ ደብረ ሲና ወወሀበ ሕገ ለሙሴ ወከደነ ር እሰ ደብር በጊሜ ወጢስ በጽልመት ወነፋስ ወበድምጸ ቃለ አቅርንት ይጌሥጽ ለእለ ይቀውሙ በፍርሃት። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፱.ውእቱኬ ዘወረደ ኀቤኪ ኦ ደብር ነባቢት በትሕትና መፍቀሬ ሰብእ ተሰብአ እምኔኪ ዘእንበለ ውላጤ ፍጹመ ሥጋ ነባቢ ዘከማነ በመንፈሰ ጥበብ አምላክ ኀደረ ላዕሌሃ ኮነ ፍጹመ ሰብአ ከመ ያድህኖ ወይስረይ ኃጢአቶ ለአዳም ወያንብሮ ውስተ ሰማያት ወያግብኦ ኀበ ዘትካት መንበሩ በዕበየ ሣህሉ ወምሕረቱ ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፲. ዕበያ ለድንግል ኢይትከሃል ለተነግሮ እስመ እግዚእ ኀረያ መጽአ ወኀደረ ላዕሌሃ ዘየኀድር ውስተ ብርሃን ኀበ አልቦ ዘይቀርቦ ተጸውረ በከርሣ ፱ተ አውራኃ ዘኢይትረአይ ወዘኢ ይታዐወቅ ወለደቶ ማርያም እንዘ ድንግል ይእቲ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፲፩. ዘውእቱ ዕብን ዘርዕየ ዳንኤል ነቢይ ዘተበትከ እምደብር ነዋኅ ዘእንበለ እድ ዘውእቱ ቃል ዘወጽአ እምኀበ አብ መጽአ ወተሰብአ እምድንግል ዘእንበለ ዘርአ ብእሲ ወአድኀነነ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፲፪.ኮንኪአጽቀ ንጹሐ ወሙዳየ አሚን ርትዕት ሃይማኖቶሙ ለቅዱሳን አበዊነ ኦ ንጽሕት ወላዲተ አምላክድንግል ኅትምት ወለድኪ ለነ ቃለአብኢየሱስ ክርስቶስ  መጽአ ለመድኃኒትነ። ሰአሊ ለን ቅድስት

፲፫. አንቲ እሙ ለብርሃን ክብርት ወላዲተ እግዚእ አንተ ጾር ኪዮ ለቃል ዘኢይትረአይ እምድኅረ ወለድኪ ኪያሁ ነበርኪ በድንግልና በስብሐት ወበባርኮት ያአብዩኪ። ሰአሊ ለነ ቅ.

፲፬. አይ ልሳን ዘይክል ነቢበ ዘይትነገር በእንቲአኪ ኦ ድንግል ንጽሕትእሙ ለቃለ አብ ኮንኪ መንበሮ ለንጉሥ ለዘይጸውርዎ ኪሩቤል ናስተበጽአኪ ኦ ቡርክት ወንዘክር ስመኪ በኩሉ ትውልደ ትውልድ ኦ ርግብ ሠናይት እሙ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፲፭.ተፈሥሒ ኦ ማርያም እም ወአመት እስመ ለዘውስተ ሕጽንኪ ይሴብሕዎ መላእክት ወኪሩቤል ይሰግዱ ሎቱ በፍርሃትወሱራፌልዘእንበለ ጽርአት ይሰፍሑ ክነፊሆሙ ወይብሉ ዝንቱ ውእቱ ንጉሠ ስብሐት መጽአ ይሥረይ ኃጢአተ ዓለም በዕበየ ሣህሉ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

8.ወደ ደብረ ሲና የወረደ ለሙሴ ሕግን የሰጠ የተራራውን ራስ በጽጋግ በጢስ በጨለማና በነፋስ የሸፈነ ፈርተው የቆ ሙትንም በነጋሪቶች ድምጽ የገሰጸ የአብ አካላዊ ቃል ነው::  ቅድስት ሆይ ለምኝልን

9.በትሕትና የተናገርሽ ተራራ ሆይ ይኸውም ወደ አንቺ የወረ ደው ነው ሰውን የወደደ እርሱ ያለመለወጥ በአንቺ ሰው ሆነ እንደ እኛ በሚናገር ሥጋ ፍጹም ሆኖ አምላክ በመንፈስ ቅዱስ በማሕጸንዋ አደረና ፍጹም ሰው ሆነ። አዳምን ያድነው ዘንድ ኃጢአቱንም ያስተሠርይለት ዘንድ በሰማያት(በሰማያዊ መዓርግ) ያኖረው ዘንድ በቸርነቱና በይቅርታው ብዛት ወደ ቀድሞ ቦታው ይመልሰው ዘንድ። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

10. የድንግል ገናንነቷ ሊናገሩት አይቻልም ጌታመርጧታልና የሚቀርበው በሌለ ብርሃን ውስጥ የሚኖር እርሱ መጥቶ አደረ ባት። ዘጠኝ ወር በማኅጸንዋ አደረ። የማይ ታይና የማይመረ መር (ታይቶ የማይታወቅ) እርሱን በድንግልና ወለደችው። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

11. ነቢዩ ዳንኤል ያየው ያለ እጅ ከረጅም ተራራ የተፈነቀለው ያ ደንጊያ ከአብ ዘንድ የወጣው ቃል ነውና ። መጥቶ ያለ ወንድ ዘር ከድንግል ተወልዶ አዳነን። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

12.እንደ ንጹሕ ጫፍ ሆንሽ የሃይማኖትም መገኛ ነሽ የቀናች የቅዱሳን አባቶቻችን ሃይማኖታቸው ነሽ አምላክን የወለድሽና በድንግልና የታተምሽ ንጽሕት ሆይ የአብን  ቃል ወለድሽልን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን መጣ። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

13.የከበርሽ ጌታን የወለድሽ ሆይ የማይታይ ቃልን የተሸከም ሽው የብርሃን እናቱ አንቺ ነሽ እሱን ከወለድሽው በኋላ በድን ግልና ኖረሻልና በፍጹም ምስጋና ያገኑሻል። ቅድስት ሆይ ለም

14.የአብ ቃል እናቱ ንጽሕት ድንግል ሆይ ስለአንቺ የሚነገ ረውን ነገር መናገር የሚቻለው  ምን አንደበት ነው?ኪሩቤል ለሚሸከሙት ንጉሥ ዙፋኑ/ማደሪያው ሆንሽ የተከበርሽ ሆይ እናመሰግንሻለን የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ መልካሟ ርግብ ሆይ ስምሽን በልጅ ልጅ እንጠራለን። ቅድስት ሆይ.ለ.

15.እናትና ገረድ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ። የታቀፍሽውን መላእክት ያመሰግኑታልና ኪሩቤልም በፍርሃት ይሰግዱለታ ልና ሱራፌልም ያለማቋረጥ ክንፋቸውን ዘርግተው የሚመ ሰገን ንጉሥ/የክብር ባለቤት/ይህ ነው በይቅርታው ብዛት የዓ ለምን ኃጢአት ያሥተሰርይ ዘንድ የመጣው ይህ ነው ይላሉ። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

## ውዳሴሃ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ ዘይትነበብ በእለተ ረቡዕ

፩.ኲሉ ሠራዊተ ሰማያትይብሉ ብፅዕት አንቲ ሰማይ ዳግሚት ዲበ ምድር ኆኅተ ምሥራቅ ማርያም ድንግል ከብካብ ንጹሕ ወመርዓ ቅዱስ ነጸረ አብ እምሰማይ ወኢረከበ ዘከማኪ ፈነወ ዋሕዶ ወተሰብአ እምኔኪ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፪.ኲሉ ትውልድ ያስተበፅዑኪ ለኪ ለባሕቲትኪ ኦ እግዝእትነ ወላዲተ አምላክ

ተነበዩ ላዕሌኪ ዐቢያተ ወመንክራተ ኦ ሀገረ እግዚአብ ሄር እስመ ኮንኪ አንቲ ማኅደረ ለፍሡሓን ኲሎሙ ነገ ሥተ ምድር የሐውሩ በብርሃንኪ ወአሕዛብኒ በጸዳልኪ ኦ ማርያም ኲሉ ትውልድ ያስተበጽዑኪ ወይሰግዱ ለዘ ተወልደ እምኔኪ ወያዐብይዎ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፫. አንቲ ዘበአማን ደመና እንተ አስተርአይኪ ለነ ማየ ዝናም ትእምርተ ዋሕዱ ረሰየኪ አብ መንፈስ ቅዱስ ኀደረ ላዕሌኪ ወኃይለ ልዑል ጸለለኪ ኦ ማርያም አማን ወለድኪ ቃለ ወልደ አብ ዘይነብር ለዓለም መጽአ ወአድኀነነ እምኃጢአት ዐቢይ ውእቱ ክብር ዘተውህበ ለከ ኦ ገብርኤል መልአክዜናዊ ፍሡሓ ገጽ ሰበከ ለነ እግዚእ ዘመጽአ ኀቤነ ወአብሠርካ ለማርያም ድንግል ዘእንበለ ርስሐት ወትቤላ ተፈሥሒ ኦ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሄር ምስሌኪ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፬. ረከብኪ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ኀደረ ላዕሌኪ ወኃይለ ልዑል ጸለለኪ ኦ ማርያም አማን ወለድኪ ቅዱሰ መድኅኑ ለኲሉ ዓለም መጽአ ወአድኀነነ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፭.ግብረ ድንግል ይሴብሕ ልሳንነ ዮም ንወድሳ ለማርያም

ወላዲተ አምላክ በእንተ ዘተወልደ እምኔሃ በሀገረ ዳዊት እግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ንዑ ኲልክሙ አሕዛብ ናስተብፅዓ ለማርያም እስመ ኮነት እመ ድንግለ ወጽሙረ።

ተፈስሒ ኦ ድንግል ንጽሕት እንተ አልባቲ ርኩስ ዘመጽአ ቃለ አብ ወተሰብአ እምኔሃ ተፈስሒ ኦ ሙዳይ እንተ አልባቲ ነውር ፍጽምተ ዘአልባ ርስሐት ተፈስሒ ኦ ገነት ነባቢት ማኅ

ደሩ ለክርስቶስ ዘኮነ ዳግማይ አዳም በእንተ አዳም ቀዳሚ ብእሲተፈስሒ ኦ ጸዋሪቱ ለዋሕድ ለዘኢተፈልጠ እምኅጽነ አቡሁ ተፈስሒኦ ከብካብ ንጹህ ሥርግው በኲሉ ስነ ስብሐት መጽአ ወተሰብአ እምኔኪ ተፈስሒ ኦ ዕፀ ጳጦስ እንተ ኢያ ውአያ እሣተ መለኮት ተፈስሒ ኦ አመት ወእም ድንግል ወሰማይ ሰማያዊ እንተ ፆረት በሥጋ ዘይጼዐን ዲበ ኪሩቤል ወበእንተዝ ንትፌሣሕ ወንዘምር ምስለ መላእክት ቅዱሳን በፍ ሥሓ ወበኃሴት ወንበል ስብሐት ለእግዚአብሄር በሰማያት ወሰ ላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ እስመ ኪያኪ ሠምረ ዘሎቱ ክብር ወስብሐት። ሰአሊ ለነ ቅድስት

## ረቡዕ የሚጸለይ አምላክን የወለደች የድንግል ማርያም ምስጋና ሦስተኛ ክፍል

1.የምድር ሁለተኛ የሆንሽ ሰማይ ሆይ የሰማያት ሠራዊት /መላእክት/ ንዕድ ነሽ ይላሉ፤ ድንግል ማርያም የምሥራቅ ደጅ ናት።ሙሽራዋ ንጹሕ የሆነ ንጽሕት የሰርግ ቤት ናት። አብ በሰማይ አይቶ እንዳንቺ ያለ አላገኘምና አንድ ልጁን ላከው በአንቺም ሰው ሆነ። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

2.አምላክን የወለድሽ እመቤታችን ሆይ ትውልድ ሁሉ አንቺን ብቻ ያመሰግኑሻል

የእግዚአብሄር ሀገር /ከተማ/ ሆይ ነቢያት ድንቅ ድንቅ ነገርን ተናገሩልሽ ደስ የተሰኙ የጻድቃን ማደሪያ ሆነሻልና የምድር ነገስታት ሁሉ በብርሃንሽ ይሄዳሉ ሕዝቡም/ሠራዊቶቻቸውም በብርሃንሽ ይሄዳሉ ማርያም ሆይ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑ ሻል ከአንቺ ለተወለደውም ይሰግዱ ለታል ያገኑታልም። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

3. የዝናም ውሃ የታየብሽ የእውነትደመና አንቺ ነሽ ። አብ የልጁ ምልክት አደረገሽ መንፈስ ቅዱስ አደረብሽየልዑልኃይል ጋረደሽ ማርያም ሆይ ለዘለዓለም የሚኖር የአብን ልጅ ቃልን የወለድሽልን መጥቶም ከኃጢአት አዳነን።ደስ የተሰኘህ ሆነህ ምሥራችን የተናገርክመልአኩ ገብርኤልሆይ የተሰጠህ ክብር ታላቅ ነው ወደ እኛ የመጣ የጌታን ልደት ነገርኽን ለድንግል ማርያም ጸጋን የተመላሽ ሆይ እግዚአብሄር ካንቺ ጋር ነውና ደስ ይበልሽ ብለህ አበሰርካት። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

4.ጸጋን አገኘሽ መንፈስ ቅዱስ አደረብሽ የልዑል ኃይልም ጋረገሽ /ጸለለብሽ/ ማርያም ሆይ በእውነት ቅዱስን ወለድሽ።ዓለምን ሁሉ የሚያድን መጥቶ አዳነን። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

5.አንደበታችን የድንግልን ሥራ ያመሰግናል ጌታችንናመድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዳዊት አገር ከእርሷ ስለተወለደ አምላክን የወለደች ማርያምን ዛሬ እናመስግናት አሕዛብ ኑ ማርያምን እናመስግናትእናትና ድንግልን ሁለቱንም ሆናለችና ርኩሰት የሌለብሽና የአብ ቃል መጥቶ ከአንቺ ሰው የሆነ ንጽሕት ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ፤ ነውር የሌለብሽ ፍጽም ትና ጉድፍ የሌለብሽ ሙዳይ ሆይ ደስ ይበልሽ፤ ስለቀደመ ሰው አዳም ሁለተኛ አዳም የሆነ የክርስቶስ ማደሪያው የምት ናገርው ገነት ሆይ ደስ ይበልሽ፤ ከአባቱ ያልተለየ አንድ እሱን የተሸከምሽ ሆይ ደስ ይበልሽ፤ በክብር ጌጽ ሁሉ እርሱ መጥቶ ሰው የሆነብሽ ንጽሕት የሠርግ ቤት ሆይ ደስ ይበልሽ የመለኮት እሣት /ባሕርይ/ ያላቃጠለሽ ዕፀ ጳጦስ ሆይ ደስ ይበልሽ፤ በኪሩቤል ላይ የሚቀመጠውን ሰማያዊ /መለኮትን/ በስጋ የተሸከምሽ ገረድና እናት ድንግልና ሰማይ ሆይ ደስ ይበ ልሽ፤ ስለዚህ ንጹሃን ከሆኑ መላእክትጋራ በፍጹም ደስታ ደስ ተሰኝተን እናመስግን በሰማይም ለእግዚአብሄር ምስጋና ይሁን በምድርም እርቅ ይሁን እንበል ክብርና ምሥጋና /ጌትነት/ ያለው እርሱ አንቺን ወዷልና። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

፮.የዐቢ ክብራ ለማርያም እምኵሎሙ ቅዱሳን እስመ ድልወ ኮነት ለተወክፎ ቃለ አብ ዘይፈርህዎ መላእክት ወየአኵትዎ ትጉሃን በሰማያት ፆረቶ ማርያም ድንግል በከርሣ ይእቲ ተዐቢ እምኪሩቤል ወትፈደፍድ እምሱራ ፌል እስመ ኮነት ታቦተ ለአሐዱ ዘእም ቅድስት ሥላሴ ዛቲ ይእቲ ኢየሩሳሌም ሀገሮሙ ለነቢያት ወማኅደረ ፍስሐሆሙ ለኵሎሙ ቅዱሳን ሕዝብ ዘይነብር ውስተ ጽልመት ወጽላሎተ ሞት ብርሃን አቢይ ሠረቀ ላዕለሆሙ እግዚአብሄር ዘየአርፍ በቅዱሳኒሁ ተሰብአ እምድንግል ለመድኃኒተ ዚአነ ንዑ ርእዩ ዘንተ መን ከረ ወዘምሮ ዘምሩ በእንተ ምሥጢር ዘተከሥተ ለነ እስመ ዘኢይሰባእ ተሰብአ ቃል ተደመረ ወዘአልቦ ጥንት ኮነ ቅድመ ወለዘአልቦ መዋዕል ኮነ ሎቱ መዋ ዕል ዘኢይትአወቅ ተከስተ ወዘኢይትረአይ ተርእየ ወልደ እግዚአብሄር ሕያው ጥዩቀ ኮነ ሰብአ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘትማልም ወዮም ወከመ ውእቱ እስከ ለዓለም አሐዱ ህላዌ ሎቱ ንስግድ ወንሰብሖ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

6. ከቅዱሳን ክብር የማርያም ክብር ይበልጣል የአብን ቃል ለመቀበል በተገባ ተገኝታለችና መላእክት የሚፈ ሩትን ትጉሆች በሰማያት የሚያመሰግኑትን ድንግል ማርያም በማሕጸኗ ተሸከመችው። ይህች ከኪሩቤል ትበልጣለች ከሱራፌልም ትበልጣለች።ከሦስቱ አካል ለአንዱ ማደሪያ ሆናለችና የነቢያት ሀገራ ቸው ኢየሩሳሌም ይህች ናት። ለቅዱሳን ሁሉ የደስታቸው ማደሪያ ናት በጨለማና በሞት ጥላ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ታላቅ ብርሃን ወጣላቸው በቅዱሳን ላይ የሚያድር እግዚ አብሄር እኛን ለማዳን ልዩ ከሆነች ድንግል ሰው ሆኗልና ኑ ይህን ድንቅ እዩ ስለተገለጠልን ምሥጢር ምስጋና አቅርቡ ሰው የማይሆን ሰው ሆኗልና ቃል ተዋህዷልና ጥንት የሌ ለው ስጋ ጥንታዊ ቀዳማይ ሆነ ዘመን የማይቆጠርለት /መለኮት/ ዘመን ተቆጠረለት የማይታወቅ ተገለጠ የማ ይታይ ታየ የሕያው የእግዚአብሄር ልጅ በእርግጥ ሰው ሆነ። ትላንት የነበረው ዛሬም ያለው መቼም የሚኖረው ኢየሱስ ክርስቶስ እንሰግድለትና እናመሰግነው ዘንድ አንድ ባሕርይ ነው። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

፯. ሕዝቅኤል ነቢይ ኮነ ስምዐ በእንቲአሃ ወይቤ ርኢኩ ኆኅተ በምሥራቅ ኅቱም በዐቢይ መንክር ማኅተም አልቦ ዘቦአ ዘእንበለ እግዚአ ኃያላን ቦአ ውስቴታ ወወጽአ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

7.ነቢዩ ሕዝቅኤል ስለ እርሷ መሰከረ ድንቅ በሆነ ታላቅ ቁልፍ የተዘጋች ደጅ ከምሥራቅ አየሁ አለ ከኃያላን ጌታ በቀር ወደ እርሷ ገብቶ የወጣ የለም። ቅድስት ሆይ ለም ኝልን

፰.ኆኅትሰ ድንግል ይእቲ እንተ ወለደት ለነ መድኅነ እምድኅረ ወለደት ኪያሁ ነበረት በድንግልና ከመ ትካት ቡሩክ ውእቱ ፍሬ ከርሥኪ አ ወላዲተ እግዚእ ዘመጽአ ወአድኃነነ እምእደ ጸላኢ ዘአልቦ ምሕረት አንቲ ፍጽምት ወቡርክት ረከብኪ ሞገሰ በኀበ ንጉሠ ስብሐት አምላክ ዘበአማን ለኪ ይደሉ እምኵሎሙ እለ ይነብሩ ዲበ ምድር ቃለ አብ መጽአ ወተሰብአ እምኔኪ ወአን ሶሰወ ምስለ ሰብእ እስመ መሐሪ ውእቱ ወመፍ ቀሬ ሰብእ አድኃነ ነፍሳቲነ በምጽአቱ ቅዱስ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

8.ኆኅትም /ደጅም/ መድኃኒታችንን የወለደች ድንግል ናት። እርሱን ከወለደች በኋላ እንደ ቀድሞው በድንግልና ኖራለችና መጥቶ ምሕረት ከሌለው ጠላት እጅ ያዳነን ጌታን የወለድሽ ሆይ የማኅፀንሽ ፍሬ የተባረከ ነው። አንቺ ፍጽምትና የተባረክሽ ነሽ የእውነት አምላክ በሆነ በክብር ባለቤት ዘንድ ባለሟ ልነትን አግኝተሻልና በምድር ላይ ከሚኖሩ ሁሉ ይልቅ ገናንነትና ክብር ለአ ንቺ ይገባል የአብ ቃል መጥቶ በአንቺ ሰው ሆነ ከሰው ጋርም ተመላለሰ፤መሐሪ ይቅር ባይ ሰውን ወዳጅ ነውና በልዩ አመጣጡ አዳነን ። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

## ውዳሴሃ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ ዘይትነበብ በእለተ ሐሙስ

፩. ዕፀ እንተ ርዕየ ሙሴ በነደ እሣት ውስተ ገዳም ወአዕፁቂሃ ኢትውዒ ትመስልማርያም ድንግልዘእንበለ ርኩስ ተሰብአ እምኔሃ ቃለ አብወኢያውአያ እሣተ መለ ኮቱ ለድንግል እምድኅረ ወለደቶ ድንግልናሃ ተረክበ ወመለኮቱ ኢተወለጠ ኮነ ወልደ እጓለ እመሕያው አምላክ ዘበአማን መጽአ ወአድኃነነ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፪. ናዐብየኪ ኩልነ ኦ እግዝእትነ ወላዲተ አምላክ እስመ ሳህልኪ ይኩን ላዕለ ኩልነ

ትምክህተ ኩልነ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ዘበእንቲኣሃ ተሥዕረ ዘቀዳሚ መርገም እንተ ሃደረት ዲበ ዘመድነ በዕልወት ዘገብረት ብእሲት በልአት እምዕፀ በእንተ ሔዋን ተዐ ፅወ ኆኅተ ገነት ወበእንተ ማርያም ድንግል ተርኅወ ለነ ዳግመ ከፈለነ ንብላዕ እምዕፀ ሕይወት ዘውእቱ ሥጋሁ ለክርስቶስ ወደሙ  ክቡር በእንተ ፍቅረ ዚአነ መጽኣ ወአድኃነነ አይ ልቡና ወአይ ነቢብ ወአይ ሰሚዕ ዘይክል አእምሮ ዝንቱ ምሥጢር መንክራተ ዘይትነበብ ላዕሌሃ እግዚአብሄር መፍቀሬ ሰብእ  ፩ዱ ውእቱ ባሕቲቱ ቃለ አብ ዘሃሎ እምቅድመ ዓለም በመለኮቱ እንበለ  ሙስና እም፩ዱ አብ መጽአ ወተሰብአ ወልድ ዋሕድ እምቅድስት እሙ እምድህረ ወለደቶ ኢማሰነ ድንግልናሃ ወበእንተዝ ግህደ ኮነት ከመ ወላዲተ አምላክ ይእቲ ኦ ዕሙቅ ብዕለ ጥበቡ ለእግዚአብሄር ከርሥ ዘፈትሐ ላዕሌሃ ትለድ በፃዕር ወሕማም ወኀዘነ ልብ ወኮነት ፈልፈለ ሕይወት ወወለደት ዘእንበለ ዘርአ ብእሲ ዘይሥዕር መርገመ እምዘመድነ ወበእንተዝ ንሰብሖ እንዘ ንብል ስብሐት ለከ ኦ መፍቀሬ ሰብዕ ኄር ወመድኃኔ ነፋሳቲነ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፫.ኦ ዝ መንክር ወዕፁብኃይለ ከርሣ ለድንግል ወላዲተ አምላክ ዘእንበለ ዘርእ ስምዐ ኮነ መልአክ ዘአስተርአዮ ለዮሴፍ እንዘ ይብል ከመዝ እስመ ዘይትወለድ እምኔሃ እመንፈስ ቅዱስ ቃለ እግዚአብሄር ውእቱ ተሰብአ ዘእ ንበለ ውላጤ ወለደቶ ማርያም ምክዕቢተ ዝንቱ ፍስሓ ወይቤ ትወልዲ ወልደ ወይሰመይ አማኑኤል ዘበትርጓ ሜሁ እግዚአብሄር ምስሌነ ወዓዲ ይሰመይ ኢየሱስሃ ዘያድኅኖሙ ለሕዝቡ እምኃጢአቶሙ ያድኅነነ በኃይሉ ወይስረይ ኃጢአተነ እስመ ጥዩቀ አእመርናሁ ከመ አምላክ ውእቱ ዘኮነ ሰብአ ሎቱ ስብሐት እስከ ለዓለም ኦ ዝ መንክር ልደተ አምላክ እማርያም እምቅድስት ድንግል አግመረቶ ለቃል ኢቀደሞ ዘርእ ለልደቱ ወኢ አማሰነ በልደቱ ድንግልናሃ እምኀበ አብ ወጽአ ቃል ዘእንበለ ድካም ወእምድንግልተወልደ ዘእንበለ ሕማም ሎቱ ሰገዱ ሰብአ ሰገል አምጽኡ ዕጣነ ከመ አምላክ ውእቱ ወርቀ እስመ ንጉስ ውእቱ ወከርቤ ዘይትወሀብ ለሞቱ ማሕየዊ በእንቲአነ ተወክፈ በፈቃዱ ፩ዱ ውእቱ ባሕ ቲቱ ኄር ወመፍቀሬ ሰብእ።  ሰአሊ ለነ ቅድስት

## ሐሙስ የሚጸለይ አምላክን የወለደች የእመቤታችን የድንግል ማርያም ምስጋና አራተኛ ክፍል

1. ርኩሰት የሌለባት ድንግል ማርያም ሙሴ በበረሃ በነደ እሳት ጫፎቿ ሳይቃጠሉ ያያት ዕፅን ትመስላለች የአብ ቃል በርስዋ ሰው ሆኗልና እሳተ መለኮቱ /የመለ ኮቱ ባህርይ/ አላቃጠላትምና ከወለደችውም በኋላ ድን ግልናዋ አልተለወጠምና ሰውም ቢሆን መለኮቱ አልተ ለወጠም በእውነት አምላክ ነውና በእውነት አምላክ የሆነ መጥቶ አዳነን። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

2. አምላክን የወለድሽ እመቤታችን ሆይ ሁላችን እናገንሻለን ይቅርታሽ ለሁላችን ይሆን ዘንድ ነውና ። ሔዋን እንጨት በልታ ባደረገችው ዓመፅ በባሕርያችን ያደረ የቀድሞው እርግማን በእርስዋ የጠፋልን አምላክን የወለደች ድንግል ማርያም የሁላችን መመኪያ ናት ። ስለ ሔዋን የገነት ደጅ ተዘጋ ዳግመኛም ስለ ድንግል ማርያም ተከፈተልን ከዕፀ ሕይወት እንበላ ዘንድ አደለን ይኸውም እኛን ስለመውደድ መጥቶ ያዳነንየክርስቶስ ክቡር ሥጋው ክቡር ደሙ ነው ሰለ እርሷድንቅ ሆኖ የሚነገረውን ይህን ምስጢር ማወቅ የሚቻለው ምን ልቡና ነው?መናገር የሚቻለው ምን አንደበት ነው?መስማት የሚቻለው ምን ጆሮ ነው? ሰውን የሚወድ እግዚአብሄር አንድ ብቻ የሆነ አምላክነቱ ሳይለወጥ ከዓለም በፊት የነበረ የአብ ቃል ከአብ ዘንድ መጥቶ ልዩ ከሆነች እናቱ ሰው ሆነ ከወለደ ችው በኋላም ድንግልናዋ አልተለወጠም ስለዚህም አምላ ክን የወለደች እንደሆነች ታወቀች እግዚአብሄር የጥበቡ ስፋት ምን ይጠልቅ? በጻእር በምጥ በልብ ጋር ትወልድ ዘንድ የፈረደባት ማኅፀን የሕይወት መገኛ ሆነች ከባሕር ያችን እርግማንን የሚያጠፋልንን ያለ ወንድ ዘር ወለደች ልን ስለዚህም ሰውን የምትወድ ሆይ ክብር ላንተ ይገባል ቸርና የሰውነታችንም መድኃኒት ነህ እያልን እናመስግነው ቅድስት ሆይ ለምኝልን

3. ያለ ወንድ ዘር አምላክን የወለደች ድንግል የማኅፀንዋ ሥራ ምን ይደንቅ? ለዮሴፍ የታየው መልአኩ ከእርስዋ  በመንፈስ ቅዱስ የሚወለደው ያለ መለወጥ ሰው የሚሆ ነው የእግዚአብሄር ቃል ነው ብሎ መስክሯልና ማርያም የዚህ ደስታ ዕፅፍ የሆነ እርሱን ወለደችው መልአኩ ልጅ ትወልጃለሽ ስሙም አማኑኤል ይባላል አላት። ትርጓሜ ውም እግዚአብሄር ከእኛ ጋር ሆነ ማለት ነው። ዳግመኛ ወገኖቹን ከኀጢአታቸው የሚያድናቸው ኢየሱስ ይባላል በችሎታው /በኃይሉ/ ያድነን ዘንድ ኀጢአታችንንም ያስ ተሥርይልን ዘንድ ለዘላለም ክብር ይግባውና ሰው የሆነ እርሱን አምላክ እንደሆነ በተረዳ ነገር አውቀነዋልና  ልዩ ከሆነች ድንግል ማርያም ይህ የአምላክ መወለድ ምን ይደንቅ ቃልን ወሰነችው ልደቱንም ዘር አልቀደመውም በመወለዱም ድንግልናዋን አልለወጠውም ቃል ከአብ ያለ ድካም ወጣ ከድንግልም ያለህማም ተወለደ። ሰብአ ሰገል ሰገዱለት አምላክ ነውና ዕጣን አመጡለት ንጉሥም ነውና ወርቅ አመጡለት  ስለኛ በፈቃዱ ለተቀበለው መዳኛችን ለሆነ ሞቱም ከርቤ አመጡለት ቸርና ሰውን ወዳጅ የሆነ አንድ እርሱ ብቻ ነው። ቅድስት ሆይ ለምኝልን.

፬.ኦ ዝ መንክር ነስአ ፩ደ አጽመ እምገቦሁ ለአዳም ወለሐኮ እም ኔሁ ብእሲተ ወኩሎ ፍጥረተ እጓለ እመሕያው ተውህበ እግዚአ ቃለ አብ ተሰብአ እምቅድስት ድንግል ወተሰምየ አማኑኤልወበእ ንተዝ ንስእል ኅቤሃ ኩሎ ጊዜ ከመ ታስተሥሪ በእንቲ አነ ኅበ ፍቁር ወልዳ ኄርት ይእቲ በኀበ ኩሎሙ ቅዱሳን ወሊቃነ ጳጳ ሳት እስመ አምጽአት ሎሙ ዘኪያሁ ይጸንሁ ወለነቢያትኒ አም ጽአት ሎሙ ለዘበእንቲአሁ ተነበዩ ወለሐዋርያትኒ ወለደትሎሙ ዘሰበኩ በስሙ ውስተ ኩሉ አጽናፈ ዓለም ለሰማዕት ወለመሃይ ምናን ወጽአ እምኔሃ ዘተጋደሉ በእንቲአሁ ኢየሱስ ክር ስቶስ ብዕለ ጸጋ ጥበቡ ዘኢይትአወቅ ንኅሥሥ ዕበየ ሣህሉ እስመ መጽአ ወአድኃነነ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፭. መሐለ እግዚአብሄር ለዳዊት በጽድቅ ወኢይነስሕ እስመ እምፍሬ ከርስከ አነብር ዲበ መንበርከ ወሶበ ተወከፎ ውእቱ ጻድቅ ከመ እምኔሁ ይትወለድ ክርስቶስ በሥጋ ፈቀደ ይኅስስ ወይርከብ ማኅደሮ ዘእግዚአብሄር ቃል ወፈጸመ ዘንተ በአቢይ ትጋህ ወእምዝ ጸርሃ በመንፈስ ወይቤ ናሁ ሰማዕናሁ በኤፍራታ ወማኅደሮ ለአምላከ ያዕቆብ እንተ ይእቲ ቤተልሔም ዘኀረያ አማኑኤል ይትወለድ ውስቴታ በሥጋ ለመድኃኒተ ዚአነ ካዕበ ይቤላ ካልዕ እምነቢያት ወአንቲኒ ቤተልሔም ምድረ ኤፍራታ ኢትቴሐቲ እምነገሥተ ይሁዳ እስመ እምኔኪ ይወጽእ ንጉሥ ዘይርዕዮሙ ለሕዝብየ እስራኤል ኦ ዝ ነገር ለእሉ እለ ተነበዩ ዘበ ፩ዱ መንፈስ በእንተ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት ምስለ ኄር አቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ እምይእዜ ወእስከ ለዓለም።ሰአሊ ለነ ቅድስት

፮. ዳዊት ዘነግሠ ለእስራኤል አመ ይትነስኡ ላዕሌሁ ዕልዋን ፈተወ ይስተይ ማየ እምዓዘቅተ ቤተልሔም ፍጡነ ተንስኡ መላሕቅተ ሐራሁ ወተቃተሉ በውስተ ትዕይንተ ዕልዋን ወአ

ምጽኡ ሎቱ ውእተ ማየ ዘፈተወ ይስተይ ወሶበ ርእየ ውእቱ ጻድቅ ከመ አጥብኡ ወመጠዉ ነፍሶሙ ለቀትል በእንቲአሁ ከአወ ውእተ ማየ ወኢሰትየ እምኔሁ ወእምዝ ተኖለቁ ሎቱ ጽድቅ እስከ ለዓለም አማን መነኑ ሰማዕት ጣዕማ ለዛ ዓለም ወከዓዉ ደሞሙ በእንተ እግዚአብሄር ወተአገሱ ሞተ መሪረ በእንተ መንግስተ ሰማያት ተሣሃለነ በከመ ዕበየሣህልከ።

ሰአሊ ለነ ቅድስት

፯. አሐዱ ዘእምቅድስት ሥላሴ ርእዮ ትሕትናነ አጽነነ ሰማየ ሰማያት መጽአ ወኀደረ ውስተ ከርሰ ድንግል ወኮነ ሰብአ ከማነ ዘእንበለ ኃጢአት ባሕ ቲታ ወተወልደ በቤተ ልሔም በከመ ሰበኩ ነቢያት አድኃነነ ወቤዘወነ ወረሰየነ ሕዝበ ዚአሁ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

4. ከአዳም ጎን አንዲት ዐፅም መንሣት ምን ይደንቅ? ከእ ርሱ ሴትን ፈጠረ የሰው ፍጥረትንም ሁሉ ፈጠረ። ጌታ የአብ ቃል ተሰጠ ከልዩ ድንግልም ሰው ሆነና ዐማኑኤል ተባለ ስለዚህ ሁልጊዜ እርስዋን እንለምን ከተወደደ ልጅዋ ታማልደን ዘንድ። በቅዱሳንና በሊቃነ ጳጳሳት ሁሉ ዘንድ ቸር ናት።ደጅ የሚጠኑትን ወልዳላቸዋለችና ፤ ለነቢያትም ትንቢት የተናገሩለትን ወልዳላቸዋለችና ፤ ለሐዋርያትም እስከ ዓለም ዳርቻ በስሙ ያስተማሩለትን ወልዳላቸዋለችና ሰማዕታትና ምዕመናንም የተጋደሉለት የጥበቡ ጸጋ ብዛት የማይታወቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርስዋ ተወልዷልና የይቅ ርታውን ብዛት መርምረን እንወቅ /እንፈልግ/ መጥቶ አድኖናልና ። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

5.እግዚአብሄር የባሕርይህን ፍሬ በዙፋንህ ላይ አኖራለሁ ብሎ ለዳዊት በእውነት ማለ አይጸጸትም። ጻድቅ እርሱ ዳዊት ክርስቶስ በሥጋ ከእርሱ እንዲወለድ ባመነ ጊዜየእግዚአብሄርን ቃልማደሪያ ፈልጎ ያገኝ ዘንድ ወደደ ይህንንም በታላ ቅ ትጋት ፈጸመ ከዚህም በኋላ እነሆ በኤፍራታ ሰማነው ብሎ በመንፈስ ቅዱስ አሰምቶ ተናገረ ።ይህቺውም ዐማኑኤል እኛን ለማዳን በሥጋ ይወለድባት ዘንድ የመረጣት የያዕቆብ አምላክ ማደሪያ ናት። ዳግመኛም ከነቢ ያት አንዱ ሚክያስ አንቺ የኤፍራታ ክፍል የሆንሽ ቤተልሔም ከይሁዳ ነገሥታት መሳፍንት አገር አታንሺም።ወገኖቹ እስራኤልን የሚጠብቃቸው ንጉሥ ካንች ይወጣልና ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘለዓ ለም ድረስ ከቸር አባቱና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ምስጋና ስለተገባው ስለ ክርስቶስ በአንድ መንፈስ ቅዱስ ትንቢት የተናገሩት የነዚህ የሚክያስና የዳዊት ነገር ምን ይረቅ? ቅድስት ሆይ ለምኝልን

6. ለእስራኤል የነገሠ ዳዊት ጠላቶቹ በተነሱበት ጊዜ ከቤተልሔም ምንጭ ውሃ ይጠጣ ዘንድ ወደ ደ የጭፍሮቹ አለቆች ፈጥነው ተነሱና በጠላቶቹ ከተማ ተዋግተው ሊጠጣ የወደደውን አመጡለት ጻድቅ ዳዊትግን ጨክነው ሰውነታቸውን ስለ እር ሱ ለጦርነት ለሞት አሳልፈው እንደ ሰጡ ባየ ጊዜ ያን ውሃ አፈሰሰ ከእርሱም አልጠጣም። ከዚህ በኋላ ለዘለዓለም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት። ሰማ ዕታት የዚህችን ዓለም ጣዕም በእውነት ናቁ ደማ ቸውንም ስለ እግዚአብሄር አፈሰሱ ስለ መንግስተ ሰማያትም መራራ ሞትን ታገሡ እንደ ይቅርታህ ብዛት ይቅር በለን። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

7.ከቅድስት ሥላሴ አንዱ ወልድ መዋረዳችንን አይቶ፤ ከሰማየ ሰረማያት ወርዶ፤ ባሕርይውን ዝቅ አደረገና መጥቶ በድንግል ማኅፀን አደረ። ከብቻዋ ከኀጢአት በቀርም እንደኛ ሰው ሆነ ነቢያት ትንቢት እንደ ተናገሩለት በቤተልሔም ተወለደ። ፈጽሞ አዳነን ወገኖቹም አደረገን። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

## ውዳሴሃ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ ዘይትነበብ በእለተ ዓርብ

፩. ቡርክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከር ሥኪ ኦ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ ዘአ ንበለ ርኩስ ሠረቀ ለነ እምኔኪ ፀሐይ ጽድቅ ወ አቅረበነ ታሕተ ክነፊሁ እስመ ውእቱ ፈጠረነ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፪. ለኪ ለባሕቲትኪ ኦ እግዝእትነ ወላዲተ አምላክ

እመ ብርሃን አንቲ ናዐብየኪ በስብሐት ወበውዳሴ

ቡርክት አንቲ ተዐብዪ እምሰማይ ወትከብሪ እምድር ወላዕለ ኵሉ ሕሊናት መኑ ዘይክል ነቢበ ዕበየኪ ወአልቦ ዘይመስል ኪያኪ ኦ ማርያም መላእክት ያዐብዩኪ ወሱራ

ፌል ይሴብሑኪ እስመ ዘይነብር ዲበ ኪሩቤልወሱራፌል መጽአ ወኀደረ ውስተ ከርስኪ መፍቀሬ ሰብእ አቅረበነ ኀቤሁ ዘዚአነ ሞተ ነስአ ወእንቲአሁ ሕይወተ ወሀበነ ዘሎቱ ክብር ወስብሐት። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፫. ቡርክት አንቲ ማርያም ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ ኦ

ድንግል ወላዲተ አምላክ ምክሖን ለደናግል ዘእምቅድመ ዓለም ህልው ተሰብአ እምኔኪ ብሉየ መዋዕል ወጽአ

እምከርሥኪ ሥጋነ ነስአ ወመንፈሶ ቅዱሰ ወሀበነ ወረ

ሰየነ ዕሩያነ ምስሌሁ ብበዝኀ ኂሩቱ አንቲ ተዐብዪ እምብዙኃት አንስት እለ ነስአ ጸጋ ወክብረ ኦ ማርያም ወላ ዲተ አምላክ ሀገር መንፈሳዊት ዘኀደረ ላዕሌሃ እግዚአብ ሄር ልዑል እስመ ዘይነብር ዲበ ኪሩቤል ወሱራፌል በእራኀኪ ሐቀፍኪዮ ወዘይሴሲ ለኵሉ ዘሥጋ በብዝኃ ኂሩቱ አኀዘ አጥባተኪ ወጠበወ ሐሊበ ዘውእቱ አምላክነ መድኃኔ ኵሉ ይርዕየነ እስከ ለዓለም ንስግድ ሎቱ ወንሰብሖ እስመ ውእቱ ፈጠረነ ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፬.ማርያም ድንግልሙዳየ ዕፍረትነቅዐ ፈልፈለ ማየ ሕይ ወት ፍሬ ከርሣ አድኀነ ኵሎ ዓለመ ወሰዐረ እምኔነ መር ገመ ወገብረ ሰላመ ማእከሌነ በመስቀሉ ወበትንሳኤሁ ቅድስት አግብኦ ለብእሲ ዳግመ ውስተ ገነት። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፭.ማርያም ንጽሕትድንግል ወላዲተ አምላክ ማእምንት ሰአሊተ ምሕረት ለውሉደ ሰብእ ሰአሊለነ ኀበ ክርስቶስ ወልድኪ ይሥረይ ኃጢአተነ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

## ዐርብ የሚጸለይ አምላክን የወለደች የእመቤታችን የድንግል ማርያም ምስጋና አምስተኛ ክፍል

1. ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ የማኅፅንሽም ፍሬ የተባረከ ነው ያለ ርኩሰት አምላክን የወለድሽ  ድንግል ማርያም ሆይ እውነተኛ ፀሐይ ከአንቺ ወጣልን /ጌታ ተወለደልን/ በክንፈ ረድኤቱም አቀረበን እርሱ ፈጥሮና ልና። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

2. አምላክን የወለድሽ እመቤታችን ሆይ የብርሃን እናት ነሽና አንቺን ብቻሽን በክብር በምስጋና እናገንሻለን

የተባረክሽ አንቺ ከመላእክት ትበልጫለሽ ከደቂቀ አዳምም ትበልጫለሽ ከአሳቦች ሁሉ ትበልጫለሽ ገናንነትሽን መናገር የሚቻለው ማነው አንቺን የሚመ ስል የለምና ማርያም ሆይ መላእክት ያገኑሻል ሱራፌ ልም ያመሰግኑሻል በኪሩቤልና በሱራፌል ላይ አድሮ የሚኖር ጌታ መጥቶ በማኅጸንሽ አድርዋልና ሰውን የሚወድ ወደ እርሱ አቀረበን ክብር ምስጋና ያለው እርሱ የእኛን ሞት ተቀብሎ የእርሱን ሕይወት ለእኛ ሰጠን። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

3. የደናግል መመኪያቸው አምላክን የወለድሽ ድንግል ማርያምሆይ የተባረክሽ ነሽ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው ከዓለም በፊት የነበረ እርሱ ሰው ሆኖዋልና ከአንቺ የተወለደ ሥጋችንን ነሣ/ተዋሐደ/ መንፈስ ቅዱስንም ሰጠን በቸርነቱ ብዛት መሳዮቹ አደረገን ጸጋንና ክብርን ከተቀበሉ ብዙ ሴቶች አንቺ ትበልጫለሽ አምላክን የወ ለድሽ ማርያም ሆይ ልዑል እግዚአብሄር ያደረብሽ /የከ ተመብሽ/ ረቂቅ ከተማ ነሽ በኪሩቤልና በሱራፌል ላይ የሚኖረውን ጌታንበመኻል እጅሽ ይዘሺዋልና በቸርነቱ ብዛት ስጋዊ ፍጥረትን ሁሉ የሚመግብ እርሱ ጡትሽን ይዞ ጠባ። ይኸውም ሁሉን የሚያድን አምላካችን ነው ለዘለዓለሙ ይጠብቀናል እንሰግድለትና እናመሰግነው ዘንድ እርሱ ፈጥሮናልና። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

4. ድንግል ማርያም የሽቱ መኖሪያና የሕይወት ውሃ ምንጭ ናት የማኅፀንዋ ፍሬ ሰውን ሁሉ አድንዋልና።   ከእኛም እርግማንን አጠፋልን። በመካከላችንም ሆኖ በመስቀሉ አስታረቀን በልዩ ትንሳኤውም ሰውን ዳግ መኛ ወደ ገነት መለሰው። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

5. ንጽሕት ድንግል ማርያም የታመነች አምላክን የወለ ደች ናት። ለሰዎች ልጆችም የምሕረት አማላጅ ናት። ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ ወደ ልጅሽ ወደ ክርስቶስ ለምኝልን። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

፮.ማርያም ድንግል ትጸርሕ በቤተ መቅደስ ወትብል የአምር እግዚአብሄር ከመ አልብየ ዘአአምር ባዕድ ወኢምንትኒ ዘእን በለ ድምጸ ቃሉ ለመልአክ ዘአብሠረኒ በክብር ወይቤለኒ ሰላም ለኪ ኦ ቅድስት ድንግል ፆርኪ ዘኢይፀወር አግመርኪ ዘኢይትገመር ወአልቦ ዘያገምሮ ምንትኒ ይበዝሕ ውዳሴኪ ኦ ምልዕተ ጸጋ በኩሉ ክብር እስመ ኮንኪ አንቲ ማኅደረ ቃለ አብ አንቲ ውእቱ መንጦላዕት ስፍሕት እንተ ታስተጋብኦሙ ለመሃይምናን ሕዝበ ክርስቲያን ወትሜህሮሙ ሰጊደ ለሥሉስ ማሕየዊ አንቲ ውእቱ ዘፆርኪ ዓምደ እሳት ዘርአየ ሙሴ ዘው እቱ ወልደእግዚአብሄርመጽአ ወኃደረ ውስተ ከርሥኪ ኮንኪ ታቦቶ ለፈጣሬ ሰማያት ወምድር ፆርኪዮ በከርሥኪ ፱ተ አውራኃ። አንቲ ማእምንት ለዘኢያገምርዎ ሰማያት ወምድር ኮንኪ ተንከተመ ለዕርገት ውስተ ሰማይ ብርሃንኪ የዐቢ እም ብርሃነ ፀሐይ። አንቲ ውእቱ ምሥራቅ ዘወፅአ እምኔኪ ኮከብ ብሩህ ዘነጸርዎቅዱሳንበፍስሓ ወበኃሴት ዘፈትሐ ላዕለ ሔዋን ትለድ በፃዕር ወበሕማም አንቲሰ ማርያም ሰማዕኪ ዘይብል ተፈስሒ ኦ ምልዕተ ጸጋ ወለድኪ ለነ ንጉሠ እግዚአ ኩሉ ፍጥ ረት መጽአ ወአድኀነነ እስመ መሐሪ ውእቱ ወመፍቀሬ ሰብእ በእንተዝ ንዌድሰኪ በከመ ገብርኤል መልአክ እንዘ ንብል ቡርክት አንቲ ማርያም ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ ተፈሥሒ ኦ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሄር ምስሌኪ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

6. ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ አሰምታ ትናገር ነበር መልአኩ ቅድስት ድንግል ሆይ ሰላምታ ይገባሻል ብሎ አክ ብሮ ከነገረኝ ነገር በቀር ምንም ምን ሌላ የማውቀው ነገር እንደሌለኝ እግዚአብሄር ያውቃል አለች። የማይቻለውን ቻልሽ የማይወሰነውንና ምንም ምን የሚወስነው የሌለውን ወሰንሽ። በክብር ሁሉ ላይ ጸጋን የተመላሽ ሆይ ምስጋናሽ ይበዛል ክብርሽ ፍጹም ነው። የአብ ቃል ማደሪያ ሆነሻልና የክርስቲያን ወገኖች ምዕመናንን የምትሰበስቢያቸውና ማሕ የዊ የሚያድኑን ለሆኑ ለሥላሴ ሰጊድን/መስገድን/ የምታስተ ምሪላቸው ሰፊ መጋረጃ ሙሴ ያየውን የእሳት አምድ የተሸከ ምሽ አንቺ ነሽ ይኸውም መጥቶ በማሕፀንሽ ያደረው የእግዚ አብሄር ልጅ ነው። ሰማይንና ምድርን ለፈጠረ ጌታ ማደሪያ ሆንሽ። ዘጠኝ ወር በማሕፀንሽ ተሸከምሽው ሰማይና ምድር ለማይወስኑት የታመንሽ አንቺ ነሽ። ከምድር ወደ ሰማይ ለማ ረግ መሰላል ሆንሽ። ብርሃንሽ ከፀሐይ ብርሃን ይበልጣል። ቅዱሳን በፍጹም ደስታ ያዩት ኮከብ ከአንቺ የተወለደ ምስራቅ አንቺ ነሽ። ይኸውም በጻዕርና በምጥ ትወልድ ዘንድ በሔዋን የፈረደባት ነው። አንቺ ማርያም ግን ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ የሚል ቃልን ሰማሽና መጥቶ ያዳነን የፍጥረት ሁሉ ገዥ የሆነ ንጉሥን ወለድሽልን መሐሪ ነው ሰውንም ወዳጅ ነው።ስለዚህ ማርያም ሆይ የተባረክሽ ነሽ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው ጸጋን የተመላሽ ሆይ እግዚአብሄር ከአንቺ ጋር ነውና ደስ ይበልሽ እያልን መልአኩ ገብርኤል እንዳመሰገነሽ እናመሰግንሻለን። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

ውዳሴሃ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ ዘይትነበብ በእለተ ቀዳሚት ሰንበት

፩. ንጽሕት ወብርህት ወቅድስት በኩሉ እንተ ሐቀፈቶ ለእግ

ዚእ በእራኃ ወኩሉ ፍጥረት ይትፌሥሑ ምስሌሃ እንዘ ይጸርሑ ወይብሉ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፪. ተፈሥሒ ኦ ምልዕተ ጸጋ ተፈሥሒ እስመ ረከብኪ ሞገሰ ተፈሥሒ እግዚአብሄር ምስሌኪ

ናስተበፅዕ ዕበየኪ ኦ ግርምት ድንግልወንፌኑ ለኪ ፍሥሓ ምስለገብርኤልመልአክ እስመ እምፍሬ ከርሥኪ ኮነ መድኃ

ኒተ ዘመድነ ወአቅረበነ ሀበ እግዚአብሄር አቡሁ።ሰአሊ ለነ ቅድስት.

ቅዳሜ የሚጸለይ አምላክን የወለደች የእመቤታችን ድንግል ማርያም ምስጋና ስድስተኛ ክፍል

1.ንጽሕት ነሽ ብርሀትም ነሽ ጌታን በመኻል እጅሽ የያ ዝሽው ሆይ በሁሉ የተቀደስሽ ነሽ ፍጥረቱ ሁሉ ቅድስት ሆይ ለምኝልን ብለው እየጮሁ ከአንቺ ጋር ደስ ይላቸዋል። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

2. ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ ባለሟልነትን አግኝ ተሻልና ደስ ይበልሽ እግዚአብሄር ከአንቺ ጋር ነውና ደስ ይበልሽ ግርማ የለሽ ድንግል ሆይ ገናንነትሽን እናመሰግ ናለን እናደንቃለን እንደ መልአኩ ገብርኤልም ምስጋና እናቀርብልሻለን የባሕርያችን መዳን በማሕፀንሽ ተገኝቷ ልና ወደ አባቱ ወደ እግዚአብሄርም አቀረበን። ቅድስት ሆይ

፫. ከመ ከብካብ ዘአልቦ ጥልቀትመንፈስ ቅዱስ ኀደረ ላዕሌኪ ወኃይለ ልዑል ጸለለኪ ኦ ማርያም አማን ወለድኪ ቃለ ወልደ አብዘይነብር ለዓለም መጽአ ወአድኀነነ እምኃጢአት። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፬.አንቲ ውእቱ ዘመድ ዘእምሥርወዳዊትወለድኪለነ በሥጋ መድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዋሕድቃል ዘእምአብ ዘእምቅድመ

ዓለም ህልው ኀብአ ርእሶ ወነስአ እምኔኪ አርአያ ገብር።ሰአሊ ለነ ቅድስት

፭.ኮንኪ ዳግሚተ ሰማይ ዲበ ምድር ኦ ወላዲተ  አምላክ ዘእንበለ ርኩስ ሠረቀ ለነ እምኔኪ ፀሐየ ጽድቅ  ወወለድኪዮ በከመ ትንቢተ ነቢያት ዘእንበለ ዘርእ ወኢሙስና ። አቡሁ። ሰአሊ ለነ ቅድስት.

፮. አንቲ ውእቱ ደብተራ እንተ ተሰመይኪ ቅድስተ ቅዱሳን ወውስቴታ ታቦት በወርቅ ልቡጥ እምኩለሄ ወውስቴታጽላተ ኪዳንመሶበ ወርቅ እንተ መና ኅቡእ ዘውእቱ ወልደ እግዚአብሄር መጽአ ወኀደረ ኀበ ማርያም ድንግል ዘእንበለ ርኩስ ተሰብአ እምኔሃ ቃለ አብ ወወለደቶ ውስተ ዓለም ለንጉሠ ሥብሐት መጽአ ወአድኀነነ ትትፌሳሕ ገነት እመ በግዕ ነባቢ ወልደ አብ ዘይነብር ለዓለም መጽአ ወአድኀነነ እምኃጢአት። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፯. ተሰመይኪ እመ ለክርስቶስ ንጉሥ እምድኅረ ወለድኪ ኪያሁ ነበርኪ በድንግልና በመንክር ምስጢር ወለድኪዮ ለአማኑኤል ወበ እንተዝ አቀበኪ እንበለ ሙስና ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፰.አንቲ ውእቱ ሰዋስው ዘርእየ ያዕቆብ እግዚአብሄር ላዕሌሁ እስመ ፆርኪ በከርሥኪ ኀቱም ዘኢይትአወቅ እምኩለሄ ኮንኪ ለነ ሰአሊተ ኀበ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘተሰብአ እምኔኪ በእንተ መድኃኒትነ።ሰአሊ ለነ ቅድስት

፱. ናሁ እግዚእ ወጽአ እምኔኪ ኦ ቡርክት ጽርሕ ንጽሕት ያድኅን ኩሎ ዓለመ ዘፈጠረ በዕበየ ሣህሉ ንሰብሖ ወንወድሶ እስመ ውእቱ ኄር ወመፍቀሬ ሰብእ። ሰአሊ ለነ ቅድስት.

፲.ተፈሥሒ ኦ ምልዕተ ጸጋ ድንግል ዘእንበለ ርኩስ ልሕኩት ንጽ ሕት ክብረ ኩሉ ዓለም ብርሃን ዘኢትጠፍእ መቅደስ ዘኢትትነሰት በትረ ሃይማኖት ዘኢትጸንን ምስማኮሙ ለቅዱሳን ሰአሊ ለነ ኀበ ወልድኪ ኄር መድኃኒነ ይምሐረነ ወይሣሃለነ ይሥረይ ኃጢአተነ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

3. እንደ ሰርግ ቤት ጉድፍ የሌለብሽ ነሽ መንፈስ ቅዱስ አድሮብሻልና የልዑል ኃይልም ጸልሎሻልና ማርያም ሆይ ለዘለዓለም የሚኖር መጥቶ ከኀጢአት ያዳነን የአብ ልጅ ቃልን በእውነት ወለድሽ። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

4. ከዳዊት ሥር የተገኘሽ ባሕርይ/ዘር/አንቺ ነሽ መድኃኒ ታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በስጋ ወልደሽልናልና ከአብ የተ ወለደ ከዓለም በፊት የነበረ አንዱ ቃል ራሱን/ባሕርዩን/ ሰውረ ከአንቺም የተገኘን/የሰውን/ አርአያ ነሣ።  ቅድስት ሆይ ለምኝልን

5.አምላክን ያለርኩሰት የወለድሽው ሆይ የምድር ፪ተኛ ሰማይን ሆንሽ እውነተኛ ፀሐይ ከአንቺ ወጥቶልናልና እን ደ ነቢያት ትንቢትም ያለዘርና ያለመለወጥ ወለድሽው። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

6.ከተለዩ የተለየች የተባልሽ የኪዳን ጽላት ያለብሽ  የተ ሰወረ መና ያለበት የወርቅ መሶብ ያለብሽ ደብተራ ድን ኳን አንቺ ነሽ ይኸውም መና የተባለው መጥቶ በድንግል ማርያም ማኅፀን ያደረው የእግዚአብሄር ልጅ ነው የአብ ቃል በእርስዋ ሰው ሆነ መጥቶ ያዳነን የባሕርይ ንጉሥን በዓለም ውስጥ ወለደችው የሚናገር በግ የክርስቶስእናቱ ገነት ደስ ይላታል ለዘለዓለም የሚኖር የአብ ልጅ እርሱ መጥቶ ከኀጢአት አድኖናልና። ቅድስት ሆይ ለምኝልን    7. የንጉሥክርስቶስእናቱን ተባልሽ እርሱን ከወለድሽ በ ኋላ በድንግልና ኖርሽ ድንቅ በሆነ ምሥጢር/ተዋሕዶ/ ዐማኑኤልንወለድሽው ስለዚህም ባለመለወጥ አጸናሽ።ቅ.

8. እግዚአብሄር በላይዋ ተቀምጦባት ያዕቆብ ያያት መሰላል አንቺ ነሽ በሁሉ በኩል የማይመረመር እርሱን ተፈትሖ በሌለ በት ማኅፀንሽ ተሸከመሽዋልና እኛን ስለማዳን ከአንቺ ሰው በ ሆነ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ አማላጅ ሆንሽን። ቅ.ሆ.

9. የተባረክሽና ንጽሕት የሆንሽ አዳራሽ ሆይ እነሆ ጌታ የፈጠረውን ዓለም ሁሉ በይቅርታው ብዛት ያድን ዘንድ ካንቺ ወጣ /ተወለደ/ፈጽመን እናመስግነው ቸርና ሰውን  ወዳጅ ነውና። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

10. ያለርኩሰት ድንግል የሆንሽ ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበ ልሽ የዓለም ሁሉ መከበሪያ ንጽሕት ጽዋ ነሽ የማትጠፋ ፋና ነሽ የማትፈርሽ መቅደስ ነሽ የቅዱሳን መደገፊያቸው/መጠጊያቸው/ የማትለወጪ የሃይማኖት በትር ነሽ ቸር አዳኛችን ወደ ሆነ ልጅ ሽ ለምኝልን ፍጽሞ ይቅር ይለንና ይምረን ዘንድ ኀጢአታችን ንም ያስተሠርይልን ዘንድ። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

## ውዳሴሃ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ ዘይትነበብ በእለተ ሰንበተክርስቲያን ቅድስት

፩.ተሰመይኪ ፍቅርተ ኦ ቡርክት እምአንስት አንቲውእቱ ዳግሚት ቀመር እንተ ትሰመይ ቅድስተ ቅዱሳን ወውስ ቴታ ጽላተ ኪዳን ፲ቱ ቃላት እለ ተጽህፋ በአጻብኢሁ ለእግዚአብሄርቀዲሙ ዜነወነ በየውጣ እንተ ይዕቲቀዳሚ ስሙ ለመድኀኒነኢየሱስ ክርስቶስ ዘተሰብአ እምኔኪ ዘእንበለ ውላጤ ወኮነ አራቄ ለሐዲስ ኪዳን በውሂዘ ደሙ ቅዱስ አንፅሆሙ ለመሃ ይምናን ወለሕዝብ ንጹሃን።ሰ.ለነ ቅድስት.

፪. ወበእንተዝ ናዓብየኪ ኩልነ ኦ እግዝእትነ ወላዲተ አምላክ ንጽህት ኩሎ ጊዜ ንስዕል ወናንቅአዱ ሃቤኪ ከመ ንርከብ ሳህለ በሃበ መፍቀሬ ሰብዕ

ታቦት በወርቅ ልቡጥ እምኩለሄ ዘግቡር እም ዕፅ ዘኢይነቅዝ ይትሜሰል ለነ ዘእግዚአብሄርቃለ ዘኮነ ሰብአ ዘእንበለ ፍልጠት ወኢውላጤ መለኮትንጹሕ ዘአልቦ ሙስና ዘዕሩይ ምስለ አብ ወቦቱ አብሰራ ለንጽሕት ዘእንበለ ዘርዕ ኮነ ከማነ በኪነ ጥበቡ ቅዱስ ዘተሰብአ እምኔኪ ዘእንበለ ርኩስ ደመረ መለኮቶ።ሰአሊ ለነ ቅድስት

፫. መቅደስ ዘይኬልልዋ ኪሩቤል እለ ስዑላን በስዕለ እግዚአብሄር ቃል ዘተሰብአ እምኔኪ ዘእንበለ ውላጤ ኮነ ሰራዬ ኀጢአትነ ወደምሳሴ አበሳነ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፬. አንቲ ውዕቱመሶበ ወርቅንጹሕ እንተ ውስቴታ መና ኅቡዕ ኅብስት ዘወረደ እምሰማያት ወሃቤ ሕይወት ለኩ ሉ ዓለም ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፭. አንቲ ውዕቱ ተቅዋም ዘወርቅ እንተ ፆርኪ ማህቶተ ጰዳል ኩሎ ጊዜ ዘውዕቱ ብርሃኑ ለዓለም። ብርሃን ዘእ ምብርሃን ዘአልቦ ጥንት። አምላክ ዘእም አምላክ ዘበ አማን ዘተሰብዓ እምኔኪ ዘእንበለ ውላጤ ወበምጽአቱ አብርሃ ላዕሌነ ለእለ ንነብር ውስተ ጽልመት ወጽላሎተ ሞት ወአርትዓ እገሪነ ውስተ ፍኖተ ሰላም በምስጢረ ጥበቡ ቅዱስ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፮.አንቲ ውዕቱ ማዕጠንት ዘወርቅ እንተ ፆርኪ ፍሕመ እሳት ቡሩክ ዘነስአ እመቅደስ ዘይሠሪ ኃጢአተ ወይደ መስስ ጌጋየ ። ዝ ውዕቱ ዘእግዚአብሄር ቃል ዘተሰብዓ እምኔኪ ዘአዕረገ ለአቡሁ ርዕሶ እጣነ ወመስዋዕተ ሥሙረ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

## በሰንበተ ክርስቲያን እሁድ የሚጸለይ አምላክን የወለደች የድንግል ማርያም ምስጋና ሰባተኛ ክፍል

1.ከሴቶች ይልቅ ተለይተሽ የተባረክሽ ሆይ የተወደድሽ ተባልሽ ከተለዩ የተለየች በውስጧም የኪዳን የህግጽላት ያለባት የምትባይ ሁለተኛ ክፍል አንቺ ነሽ። ኪዳንም በእግዚአብሄር ጣቶች የተጻፉ አሥሩ ቃላት ናቸው ። ያለመለወጥ ከአንቺ ሰው የሆነ መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደገኛ ስሙን መጀመሪያስሙን አስቀድሞ በየውጣ ነገረን ለአዲስ ኪዳንም አስታራቂ ሆነ። በከበረ ደሙ ፈሳሽነት ወይም መፍሰስ ያመኑትንና ንጹሃን የሆኑትን ወገኖች አነጻቸው ። ቅድስት ሆይ ለምኚልን

2.ሁልጊዜ ንጽሕት የሆንሽ አምላክን የወለድሽ እመቤታችን ሆይ ሁላሽን ስለዚህ እናገንሻለን ሰውን በሚወድ በጌታ ዘንድ ይቅርታን እናገኝ ዘንድ እንለምንሻለን ወደ አንቺም እናንጋጥ ጣለን::

ከማይነቅዝ እንጨት የተቀረጸ በውስጥና በውጭ በወርቅ የተለበጠ ታቦት ያለመለየትና ያለመለወጥሰው የሆነ የእግዚአብሄርንቃል ይመስልልናል። ይኸውም መለወጥ የሌለበት ንጹሕ መለኮት ነው ከአብ ጋር የተካከለ ነው ። ለንጽሕት በራሱ አበሰራት።በልዩ ጥበቡ ያለ ወንድ ዘር እንደ እኛ ሆነ።መለኮቱን አዋሕዶ ያለ ርኩሰት በአንቺ ሰው ሆነ። ቅድስት ሆይ ለምኚልን

3. በእግዚአብሄር ስዕል የተሣሉ ኪሩቤል የሚጋርዱሽ መቅደስ አንቺ ነሽ። ንጽሕት ሆይ ያለመለወጥ ከአንቺ ሰው የሆነው ቃል ኃጢአታችንን የሚያስተሰርይልንና አበሳችንን የሚደመስስልን ሆነ። ቅድስት ሆይ ለምኚልን

4.የተሰወረ መና ያለብሽ የንጹሕ ወርቅ መሶብ አንቺ ነሽ መናም ከሰማይ የወረደውና ለዓለም ሁሉ ሕይወ ትን የሚያድለው ኅብስት ነው። ቅድስት ሆይ ለምኚልን

5. ሁልጊዜ ብርሃንነት ያለውን ፋና የተሸከምሽ የወርቅ መቅ ረዝ አንቺ ነሽ። ይኸውም ፋና የዓለም ብርሃን ነው ጥንት ከሌ ለው ብርሃንም የተገኘ ብርሃን ነው።ከእውነተኛ አምላክየተገኘ እውነተኛ አምላክ ነው። ያለመለወጥም ከአንቺ ሰው የሆነው ነው። በመምጣቱም/ሰው በመሆኑም/በጨለማና በሞት ጥላ ውስጥ ለምንኖር ለእኛ አበራልን። በልዩ የጥበቡ ምሥጢር (በሥጋዌ)የልቦናችንን እግር ወደ ሰላም መንገድ አቀናልን። ቅድስት ሆይ ለምኚልን

6.ቡሩክ ከቤተ መቅደስ ይዞሽ የወጣ እሳትነት ያለውን ፍሕም የተሸከምሽ የወርቅ ማዕጠንት አንቺ ነሽ።ፍሕም የተባለውም ኃጢአትን የሚያስተሠርይና በደልን የሚደመስስ ነው። ይኸውም ከአንቺ ሰው የሆነና ራሱን የተወደደ መስዋዕት አድርጎ ያሳረገ የእግዚአብሄር ቃል ነው። ቅድስት ሆይ ለምኚልን

፯.ተፈስሒ  ኦ ማርያም ርግብ ሰናይት ዘወለድኪ ለነ ዘእግዚአብሄር ቃለ። አንቲ ውዕቱ ጽጌ መዓዛ ሰናይ እንተ ሰርጸት እምሥርወ  እሴይ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፰.በትረ አሮን እንተ ሰረጸት ዘእንበለ ተክል ወኢሰቀይዋ

ማየ ከማሃ አንቲኒ አወላዲተ ክርስቶስ አምላክነ ዘበአማን ዘእንበለ ዘርዕ መጽዓ ወአድኅነነ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

፱. ለኪ ይደሉ  ዘእምኩሎሙ  ቅዱሳን ትስአሊ ለነ  ኦ ምልዕተ ጸጋ አንቲ ተአብዪ እም ሊቃነ ጳጳሳት ወፈድፋደ ትከብሪእም ነቢያት ብኪ ግርማ ራእይ ዘየአቢ እምግርማ ሱራፌል ወኪሩቤል።አንቲ በአማን ምክሃ ዘመድነ ወሰአ ሊት ሕይወተ ለነፍሳቲነ ሰአሊ ለነ ሃበ እግዚእነ ወመድ ሃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ያጽንአነ በርትዕት ሃይማኖት ውስተ አሚነ ዚአሁ ይጸግወነ ሳሕሎ ወምሕረቶ ይስረይ ኃጢኣተነ በብይዝኀ ምሕረቱ። ሰአሊ ለነ ቅድስት

7. የእግዚአብሄርን ቃል የወለድሽልን መልካሟ ርግብ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ ከዕሴይ ሥር የወጣሽ መዐዛሽ ያማረ አበባ አንቺ ነሽ። ቅድስት ሆይ ለምኝልን.

8.ሳይተክሏትና ውሃሳያጠጧት የለመለመች የአሮን በትር ነበረች።ያለ ዘር ሰው ሆኖ ያዳነን እውነተኛ አምላካችንን ክርስቶስንየወለድሽልን ሆይ አንቺ እንደ እርስዋ ነሽ። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

9. ጸጋን የተመላሽ ሆይ ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ትለምኝልን ዘንድ ለአንቺ ይገባሻል። አንቺ ከሊቃነ ጳጳሳት ትበልጫለሽ ከነቢያትም ከመምህራንም ትበልጫለሽ ከሱራፌልና  ከኪ ሩቤል ግርማ የሚበልጥ የመወደድ ግርማ አለሽ ። በእው ነቱ የባሕርያችን መመኪያ አንቺ ነሽ።ለሰውነታችንም ሕይ ወትን የምትለምኚ ነሽ።ወደ ጌታችንና ወደ መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምኝልን። እርሱን በማመን በቀናች ሃይ ማኖት ያጸናን ዘንድ ይቅርታውንና ምህረቱን ይሰጠን ዘንድ በቸርነቱ ብዛት ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ። ቅድስት ሆይ ለምኝልን

አንቀጸ ብርሃን

1. ኢትዮጵያዊው ቅዱስ ያሬድ የደረሰው የአምላክ እናት ምሥጋና ለእውነተኛ ፈራጅ ለአምላክ እናት ምስጋናና አገልግሎት ይገባታል፡፡

2. ቅድስት ሆይ ብፅዕት ነሽ የተመሰገንሽና የተባረክሽ ነሽ የከበርሽና ከፍ ከፍ ያለሽ ነሽ የብርሃን መውጫ የሕይወት መሰላል ነሽ አምላክን የወለድሽ እመቤታችን ድንግል ማርያም ሆይ ከተለዩ የተለየሽ የመለኮት ማደሪያ ነሽ፡፡ ከፍጥረት ሁሉ ይልቅ የተከበርሽ ሆይ አብ የወደደሽ ወልድ ያደረብሽ መንፈስ ቅዱስ ያረፈብሽ (የጸለለብሽ) ተባልሽ፡፡ በምድር ላይ ከፍተኛ አርያምን የሆንሽ ከሰማያት በላይ ያለ የአርያም የልዑል ስፍራ ምትክ አንቺ ነሽ፡፡ ቅዱሳን ነቢያት ካህናትና ነገሥታት ያንቺ ምሳሌ አድርገው በውስጧ የኪዳን የሕግ ጽላት ያለባት ቅድስተ ቅዱሳን ከተለዩ የተለየችውን ሠሩ፡፡ ቅድስት ሆይ ልጅሽ ይቅርታውን ያድለን ዘንድ ለምኝልን፡፡

3. የአምላክ ልጅ ካንቺ ሰው ስለመሆኑ ስላንቺም ከምድር ወደ አርያም ወደ መንግሥተ ሰማያት የቀረብን ሆን በአንቺና በልጅሽ ስም የቀረብን ሆን፡

4. ዐሥሩ ቃላት በጣቶቹ የተጻፉ የፍጥረት ሁሉ ጌታ ያውም ያምላክ ልጅ በማኅፀንሽ አደረ፡፡ አብ በሥልጣኑ አጸናሽ መንፈስ ቅዱስም ጸለለብሽ አነጻሽ የልዑል ኃይልም አጸናሽ፡፡ ኢየሱስም ያንችን ሥጋ ለበሰ በታላቅ ቃል ጮኸ መጽሐፍ የሕይወት ውኃ ምንጭ ከሆዱ ይፈልቃል እንዳለ ማንም የተጸማ ቢኖር ወደኔ መጥቶ ይጠጣ አለ፡፡ ቅድስት ሆይ ልጅሽ ይቅርታውን ያድለን ዘንድ ለምኝልን፡፡

5. አብ አስቀድሞ በየውጣ ነገረን የውጣ የተባሉ በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፉ ዐሥሩ ቃላት ናቸው፡፡ ልጅህ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንተ ብቻ አባቱ እንደ ሆንክ እርሱም ብቻ ልጅህ እንደሆነ አስተማረን፡፡ እንዲሁም በሰማይ እናት በምድር አባት የለም ብለን እናምናለን መምጣቱን ከአባቱና ከእውነት መንፈስ ከጳራቅሊጦስ በቀር የሚያውቅ ሳይኖር ከሰማይ ወረደ ብለን እናምናለን በማኅፀንሽ አደረና ዘጠኝ ወር ተሸከምሽው ሰማያት ደስ ተሰኙ ምድርም ደስ ተሰኘች፡፡ በልጅሽ መወለድ መልአክ ምሥራች ተናገረ፡፡ የሰማይ ጭፍሮችም መላእክትም ምስጋና በሰማይ ለእግዚአብሔር ይሁን በምድርም ላይ ሰላይ በሰውም እርሱ በሚፈቅደው እያሉ አመሰገኑ፡፡ እረኞችም በቤተልሔም ካዩትና ከሰሙት የተነሣ አደነቁ የጥበብ ሰዎች ብልሆች ሰዎች ለልጅሽ ሊሰግዱና አንቺን ሊያገለግሉ ኮከብን አይተው ከሩቅ አገር መጡ፡፡ ከምሥራቅ ጀምሮ መርቶ እስከ ቤተልሔም ያደረሳቸው ያ ኮከብ አንቺ ከሕጻንሽ ጋር ባለሽበት ቦታ ላይ ቆመ፡፡ እነዚያ ብልሆች ሰዎች አይተው በታላቅ ደስታ ደስ ተሰኙ ወደ እርሱ ወደ ሕጻንሽ ገቡና በፊቱ ቆሙ በምድር ላይ ወድቀው ሰገዱለት ሣጥናቸውንም ከፈቱና ወርቅ ዕጣን ከርቤን እጅ መንሻ አድርገው አገቡለት የወገኖችህን ልመናቸውንና መሥዋዕታቸውን ትቀበል ዘንድ ኃጢአታቸውንም ታስተሠርይላቸው ዘንድ የመጣህ አምላካችን ሆይ እጅ መንሻ አገባንልህ ለከበረ ስምህም ካንተ የተገኘውን ዕጣን አቀረብንልህ አሉት፡፡ ቅድስት ሆይ ልጅሽ ይቅርታውን ያድለን ዘንድ ለምኝልን፡፡

6. ከንጹሓን ይልቅ ንጽሕት የሆንሽ አንቺ ነሽ ከማይነቅዝ እንጨት እንደተሠራ በወርቅ እንደተጌጠና ዋጋው ብዙ በሆነ በሚያበራ ዕንቁ እንደተለበጠ ታቦት በቤት መቅደስ ውስጥ የኖርሽ የተመረጥሽ ድንግል ነሽ፡፡ እንዲህ ሆነሽ በቤተ መቅደስ ኖርሽ መላእክትም ዘወትር ምግብሽን ያመጡ ነበር መላእክት እየጐበኙሽ እንዲህ ዓሥራ ሁለት ዓመት ኖርሽ፡፡ መጠጥሽም የሕይወት መጠጥ ነበር ምግብሽም የሰማይ ኅብስት ነበር አባትሽ ዳዊት በመሰንቆ አመሰገነ በትንቢት መንፈስም በመንፈስ ቅዱስም በገና እየደረደረ እንዲህ ብሎ ዘመረ ልጄ ሆይ ስሚ እዪም ዠሮሽንም አዘንብዪ ሕዝብሽንና የአባትሽን ቤት እርሺ ንጉሡም ውበትሽን ይወዳል እርሱ ጌታሽ ነውና ለእርሱም ስገጅ ትሰግጃለሽ ቅድስት ሆይ ልጅሽ ይቅርታውን ያድለን ዘንድ ለምኝልን፡፡

7. ከንጹሓን ካልበደሉ መላእክት ወገን የሆነና በደል የሌለበት በሁሉ ጌታ ፊት የሚቆም ከደጋጐቹ መላእክት ወገን የሆነ መልአኩ ገብርኤል አበሠረሽ እንዲህም አለሽ ጸጋን ያገኘሽ ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው ከሴቶች ይልቅ የተባረክሽ ነሽ የሁሉ ገዥ በሆነ እግዚአብሔር ዘንድ ባለሟልነትን አገኘሽ፡፡ እነሆ ትፀንሻለሽ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ እርሱ ታላቅ ነው የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይባላል እግዚአብሔር አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል ለዘላለሙ የያዕቆብን ወገን ይገዛል ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም፡፡ መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል የልዑል ኃይልም ይጸልልሻል፡፡ ካንቺ የሚወለደውም ቅዱስ ነው ቅድስት ሆይ ካንቺ የተወለደው ይቅርታውን ያድለን ዘንድ ለምኝልን፡፡

8. የንጽሕና አዳራሽና ከተለዩ የተለየሽ መቅደስ አንቺ ነሽ፡፡ የብርሃን መጋረጃና የማይመረመር የክብር (የጌትነት) ዙፋን አንቺ ነሽ ቅድስት ማርያም ሆይ መንፈስ ቅዱስ መጥቶ ስላደረብሽና የልዑል ኃይል ስለጸለለብሽ ቅድስተ ቅዱሳን (ከተለዩ) የተለየች በሆነች መቅደስ መሰልንሽ የብርሃን መጋረጃ ነሽ ማለታችን ግን የአብ ቃል የሆነ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማኅፀንሽ ስለተሠወረ ነው፡፡ ይኸውም በላይ ያለ የሁሉ ጌታ ነው፡፡ መላእክትና የመላእክት አለቆች መናብር ሥልጣናት አጋዕዝት ኃይላት ሊቃናት መኳንንት የሚያመሰግኑት ነው፡፡ ልጅሽንም በዚህ ዓለም በወለድሽው ጊዜ ዓይኖቻቸው ብዙዎች የሆኑ ኪሩቤልና ክንፎቻቸው ስድስት የሆኑ ሱራፌል በበረት ውስጥ ጋረዱልሽ፡፡ የብርሃን ደመናዎችም ከበቡሽ የመላእክት አለቆች የመላእክት ሠራዊትና የሰማይ ጭፍሮች በመፍራትና በመንቀጥቀጥ በፊትሽ ቆሙ፡፡ በዚህም ዓለም ኪሩቤልና ሱራፌል በሰማያት ካለው ምስጋናቸው ወይም ከቀድሞ ምስጋናቸው ወገን ባልሆነ በሌላ (በአዲስ) ምስጋና አመሰገኑሽ ፍጥረትን ሁሉ ሰብስቦ የያዘና ፍጥረቱን ሁሉ የሚመግብ ጌታቸው በብብትሽ (በክንድሽ) ተቀምጦ ጡትሽን እንደ ሕፃን ሲጠባ ባዩ በአርያም ፈለጉና በዚህ ዓለም እንደ ቀድሞው ከአባቱና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አገኙት የጌታ ትሕትናውን ባዩ ጊዜም ዓይኖቻቸውን ወደ ላይ ወደ አርያም ከፍ ከፍ አደረጉ ክንፋቸውንም ዘርግተው ለሁሉ ጌታ ላንተ በሰማይ ምስጋና ይገባሃል፡፡ እያሉ ጌታቸውን አመሰገኑ፡፡ ዳግመኛም በዋሻ በጐል ውስጥ አንቺን ከሕጻንሽ ጋር አይተው በምድር ላይ ሰላም (ፍቅር አንድነት ሆነ) አሉ፡፡ ካንቺ የነሳውን የኛን ሥጋ ለብሶ ባዩት ጊዜም ሰውን ምንኛ ወደደው ብለው ሰገዱለት፡፡ ነቢዩ ዳዊትም እንዲህ ብሎ ትንቢት ተናገረ እግዚአብሔር በሰማይና በማደሪያው ቦታ ሆኖ በምድር ወደሚኖሩት ሁሉ ተመለከተ የሰውንም ልጆች ሁሉ አየ ንጉሥ ውበትሽን ወደደ፡፡ ዘለዓለም ማረፊያዬ ይህች ናት መርጫታለሁና በእርሷ አድራለሁ አለ፡፡ ቅድስት ሆይ ልጅሽ ይቅርታውን ያድለን ዘንድ ለምኝልን፡፡

9. የተለየሽና ደግ የሆንሽ የተመሰገንሽና የተባረክሽ የከበርሽና ከፍ ከፍ ያልሽ ሆይ የሕይወት ኅብስት ባለበት በወርቅ መሶብ መሰልንሽ፡፡ የሕይወት ኅብስትም (ይኸውም) በቀኙ ካሉ ጻድቃን ጋር ርሱን ለሚያምን በሃይማኖትም ፈቃደኛ በሆነ ልብ ከእርሱ ለሚበላም ሁሉ ሕይወትን የሚሰጥ ከሰማይ የወረደ ነው ቅድስት ሆይ ልጅሽ ይቅርታውን ያድለን ዘንድ ለምኝልን፡፡

10. የብልሃተኛ እጅ ያልሠራት በውስጧም መብራት የሚያበሩባት የወርቅ መቅረዝ አንቺ ነሽ ራሱ የአብ ብርሃን ያበራባታል እንጂ፡፡ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ወደ አንቺ መጥቶ አደረ በአምላክነቱም በዓለም ሁሉ አበራ፡፡ ጨለማን ከሰዎች ላይ አራቀ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ በብርሃኔ እመኑ ብርሃን ሳለላችሁ ተመላለሱ ብሎ በሚያድን ቃሉ አዳነን፡፡ ቅድስት ሆይ ልጅሽ ይቅርታውን ያድለን ዘንድ ለምኝልን፡፡

11. ከሁሉ ጌታ የተገኘ የሁሉ ጌታ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን በውነት የሁሉ ጌታ (የባሕርይ አምላክ) ከሆነ የተገኘ እውነተኛው የሁሉ ጌታ የተወለደ እንጂ የተፈጠረ ያይደለ በህልውና በአኗኗር ከአባቱ ጋር የተካከለ በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ በእርሱ የተፈጠረ እኛን ሰዎችን ስለማዳን የወረደው፡፡ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ፈጽሞ ሰው ሆነ፡፡ በመምጣቱም አበራልን ፍጹም ደስታንም አበሠረን (ነገረን) ወደአባቱም አቀረበን (አስታረቀን) ወደ ሕይወት ጐዳናም መራን የዘለዓለም ሕይወትንም ሰጠን፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ እርሱን በማመን ከሕጉ የተነሣ በትንቢት እያደነቀ ሕግህ በምድር ላይ ብርሃን ነው አለ፡፡ አረጋዊ ካህንና የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የጠበቀ ጻድቅና ንጹሕ ዘካርያስ ፈጽሞ አደነቀ መናገርም ጀመረና እንዲህ አለ አምላካችን በይቅርታውና በምሕረቱ በአርያም (በልዕልና) ሆኖ ጐበኘን፡፡ በጨለማና በሞት ጥላ ውስጥ ለሚኖሩትም ብርሃኑን ይገልጥላቸው ዘንድ ተወለደ ይቅር ይለን ይምረንም ዘንድ እግሮቻችንን ወደ ሰላም መንገድ አቀናልን ቅድስት ሆይ ልጅሽ ይቅርታውን ያድለን ዘንድ ለምኝልን፡፡

12. እመቤታችን ሆይ የቅዱሳንና የምእመናንን ሁሉ ጸሎት በማዕጠንታቸው ከምድር ወደ ሰማይ በሚያሳርጉ በሰማያውያን የካህናት አለቆች እጆች ውስጥ ባለ የወርቅ ማዕጠንት እንመስልሻለን፡፡ እንዲሁም ስምሽን በመጥራት የሰው ልጆችን ልመና ወደ ልዩ ሦስት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያሳርጋሉ፡፡ የወገኖችሽንም ኃጢአት ታስተሠርዪ ዘንድ ከአብ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ተፈቅዶልሻል ለሰዎች ልጆች የዘለዓለም ሕይወት ድልድይ ትሆኚ ዘንድ፡፡ የዓለም ሁሉ መድኃኒት ሆይ ለምእመናን መገኖችሽ መድኃኒታቸው ልትባይ ይገባሻል፡፡ ቅድስት ሆይ ልጅሽ ይቅርታውን ያድለን ዘንድ ለምኝልን፡፡

13. አንቺ የተባረክሽ ዕፅ ነሽ የሕይወትና የደኅንነት ዕፅ ነሽ የሕይወትና የደኅንነት ዕፅ ነሽ በገነት ውስጥ ባለው ዕፅ ሕይወት ፈንታ በዚህ ዓለም የሕይወት ዕፅ ሆንሽ ፍሬሽም የሕይወት ፍሬ ነው በሚወዱት (በሚያውቁት) በዓለም ሰዎች ዘንድ የሚሸት መልካም መዓዛ ያለው አበባ ካንቺ ታየ ይኸውም ከርቤ ሚዓ ሰሊክ የተባሉ ሽቶች በልብሶችሽ ላይ አሉ ብሎ በበገና ነቢዩ ዳዊት ትንቢት የተናገረልሽ ነው፡፡ አባትሽ ሰሎሞንም የአፍንጫሽ መዓዛ እንደ ነጭ ዕጣን መዓዛ ነው አለ እቴ መርዓት ሙሽራዬ ሆይ የታጠርሽ ተክል ነሽ መንገድሽ የታጠረች ተክል የታተመች ጉድጓድ ናት፡፡ ከሽቱ ቅመም ጋር ሽቱ አለሽ ቆዕ የሚባል ሽቱ ናርዶስ ከሚባል ሽቱ ጋር አለሽ ናርዶስ የሚባል ሽቱ መጽርይ ከሚባል ሽቱ ጋር አለሽ ቀጺመታት ቀናንሞስ የተባሉ ሽቶች ከደጋ ሽቶች ጋር አሉሽ፡፡ ከሽቶች ሁሉ የሚበልጡ ከርቤና ዐልው የሚባሉ ሽቶች ከነዚህ ሁሉ ሽቶች ጋር አሉሽ የገነት ፈሳሽ ሆይ ከደጋ የሚፈስ የሕይወት ውሃ መገናኛ ነሽ ቅድስት ሆይ ልጅሽ ይቅርታውን ያድለን ዘንድ ለምኝልን፡፡

14. ሳይተክሏትና ውሃ ሳያጠጧት የለመለመች የአሮን በትር በቤተ መቅደስ ነበረች ለካህናት ዝግጁ ያደረጋት ነበረች፡፡ አንችም በቅድስናና በንጽሕና ጸንተሽ እንደ እርስዋ በቤተ መቅደስ ኖርሽ ከቤተ መቅደስም በክብር በታላቅ ደስታ ወጣሽ፡፡ በእውነት የሕይወት ፍሬ የሆነ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ካንቺ ተገኘ፡፡ ቅድስት ሆይ ከመልአኩ እንደ ተረዳሽው ከወንድ ያለመገናኘት ልጅን አገኘሽ መልአኩ መንፈስ ቅዱስ መጥቶ ያድርብሻል የልዑል ኃይልም ይጸልልብሻል ብሎ ነግሮሽ ነበርና፡፡ ቅድስት ሆይ ልጅሽ ይቅርታውን ያድለን ዘንድ ለምኝልን፡፡

15. ጸጋን የተመላሽና የደስታ መገኛ ሆይ በልጅሽ ስም ላመን ለእኛ ለወንዶችና ለሴቶች አገልጋዮችሽ ትለምኝልን ዘንድ ይገባሻል፡፡ ይልቁንም ዓይኖቻቸው ብዙዎች ከሆኑ ከኪሩቤልና ክንፎቻቸው ስድስት ከሆኑ ከሱራፌል ግርማ የሚበልጥ የመወደድ ግርማ አለሽ እነዚያ ፊታቸውን ይሸፍናሉ፡፡ እግሮቻቸውም የትእምርተ መስቀል አምሳያዎች ናቸው ከልጅሽ መለኮት ከሚወጣው እሳት ይድኑ ዘንድ አንቺ ግን ለመለኮት ማደሪያ ሆንሽ፡፡ የመለኮት ባሕርይ አላቃጠለሽም የእሳት ነበልባልን ተሸከምሽ የመለኮት ባሕርይም አላቃጠለሽም፡፡ ሙሴ እንጨትነቷ በእሳት ሳይቃጠል ያያት ዕፀ ጳጦስን መሰልሽ፡፡ ሁለንተናው ፍጹም እሳት የሆነ የኀይላት ጌታ እንደ ዕፀ ጳጦስ አላቃጠለሽም ለክርስቲያን ወገኖች በእውነት መመኪያ የሆንሽ አንቺ ነሽ የአምላክ ልጅ ካንቺ ሰው ስለመሆኑም ባንቺ ከምድር ወደ አርያም የቀረብን ሆንን በጸሎትሽ ለሚያምኑ ምሕረትን የምትሰጪ ሆይ ለነፍሳችን ሕይወትን የምትለምኚ ነሽ ወደ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምኝልን እርሱን አባቱን መንፈስ ቅዱስን በማመን በቀናች ሃይማኖት ያጸናን ዘንድ፡፡ ይቅርታውንና ምሕረቱን ይሰጠን ዘንድ፡፡ በምሕረቱ ብዛት ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ የሁሉን ጌታ የወለድሽ ሆይ ምስጋና ይገባሻል፡፡ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለምም ምስጋናና ክብር ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ይገባል አሜን፡፡ ቅድስት ሆይ ልጅሽ ይቅርታውን ያድለን ዘንድ ለምኝልን፡፡

16. በቅዱስ ኤፍሬምና በኢትዮጵያዊው ቅዱስ ያሬድ ላይ ያደረ አምላክን የወለደች የእመቤታችን ድንግል ማርያም ልመናዋ ክብሯ የልጅዋ ቸርነት ከወዳጅዋ ------- ጋር ለዘለዓለም ይኑር አሜን፡፡

፩. ይዌድስዋ መላእክት ለማርያም በውስተ ውሳጤ መን

ጦላዕት ወይብልዋ በሃኪ ማርያም ሐዳስዩ ጣዕዋ። ይቤላ መልአክ ለማርያም ተወከፊዮ ለቃል ሃቤኪ ይመጽዕ ወበ ማኅፀነ ዚአኪ የሃድር እፎ ቤተ ነዳይ ኀደረ ከመ ምስኪን እምሰማያት ወረደ ላዕሌሃ ፈቲዎ ስነ ዚአሃ ወተወልደ እምኔሃ ።

፪. ወበሳድስ ወርኀ ተፈነወ ገብርኤል መልአክ እምሃበ እግዚአብሄር ኃበ አሃቲ ሀገር ዘገሊላ እንተ ስማ ናዝሬት ሃበ ድንግል እንተ ተፍሕረት ለብእሲ ዘስሙ ዮሴፍ ዘእምቤተ ዳዊት ወስማ ለይእቲ ድንግል ማርያም ቦአ መልአክ ሃቤሃ ወይቤላ ተፈሥሒ ፍሥሕት አ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሄርምስ

ሌኪ ቡርክት አንቲ እምአንስት። ወርእያ ደንገጸት እምቃሉ ወሃለየት ወትቤ እፎኑ ከመዝኑ እንጋ አምኃ ይትአምኑ። ወይቤላ መልአክ ኢትፍርሂ ማርያም እስመ ረከብኪ ሞገሰ በኀበ እግዚአብሄር ወናሁ ትጸንሲ ወትወልዲ ወልደ ወትሰ ምዪዮ ስሞ ኢየሱስ ውእቱ አቢይ ወይሰመይ ወልደ እግዚአ ብሄር ልዑል ወይሁቦ እግዚአብሄር አምላክ መንበረ ዳዊት አቡሁ ወይነግስ ለቤተ ያዕቆብ ለዓለም ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ ፤ ትቤሎ ማርያም ለመልአክ እፎኑ ይከውነኒ ዝንቱ እንዘ ኢየአምር ብእሴ እፎኑ ይከውነኒ አውስአመልአክ ወይቤላመንፈሰ እግዚአብሄር ቅዱስይመጽዕ ላዕሌኪ ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ ዘኒ ይትወለድ እምኔኪ ቅዱስ ውእቱ ወይሰ

መይ ወልደ እግዚአብሄር ልዑል ወናሁ ኤልሳቤጥኒ እንተ እምአዝማድኪ ይእቲኒ ጸንሰት ወረከበት ወልደ በልሕቃቲኃ ወበርስኃቲኃ ወናሁ ሳድስ ዝንቱ ወርህ ለእንተ ይብልዋ መካን እስመ አልቦ ነገር ዘይሰአኖ ለእግዚአብሄር።

ትቤሎ ማርያም ለመልአክ ነየ አመቱ ለእግዚኣ ኩሉ ነየ አመቱ ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ።

፫. ይቤላ መልአክ ሰላም ለኪ ይቤላ ገብርኤል ሰላም ለኪ

ማርያም ድንግል ሰላም ለኪ ወላዲተ አምላክ ሰላም ለኪ

ማርያም ንጽሕት ሰላም ለኪ ማርያም ቅድስት ሰላም ለኪ

ማርያም ውድስት ሰላም ለኪማርያም ፍስሕት ሰላም ለኪ ማርያም ብጽዕት ሰላም ለኪ ማርያም ቡርክት ሰላም ለኪ ማኅደረ መኮት ሰላም ለኪ ደብተራ ፍጽምት ሰላም ለኪ እኅተ መላእክት ሰላም ለኪ ወእመ ኩሉ ሕዝብ ሰላም ለኪ እግዝእትነ ማርያም ሰላም ለኪ ሰላማዊት ሰላም ሰላም ለኪ

ቀደሰኪ ለማኅደሩ ልዑልሰላም ለኪ አብደረኪ ወኀረየኪ ከመ ትኩኒዮ ማኅደሮሰላም ለኪበአልባሰ ወርቅ ዑጽፍትወኊብርት

ሰላም ለኪ ክነፈ ርግብ በብሩር ዘግቡርሰላም ለኪወገበዋቲሃኒ በሃመልማለ ወርቅ ማርያም ስርጉት ሰላም ለኪኖኅተምስራቅ

1. ይዌድስዋ መላእክት መላእክት ማርያምን በመንጦላዕት ውስጥ ያመሰግንዋ ታል ሓዳስ ጣዕዋ ለአንቺ ክብር ምስጋና ይገባሻል እያሉ መልአክ ማርያምን ቃልን ተቀበዪው አላት ከአንቺ ዘንድ ይመጣልና በማኅፀንሽም ያድራል እንዴት ከድኃ ቤት አደረ እንደ ምስኪን ከሰማያት ወርዶ የእርስዋን ባሕርይ ባሕርይ አድርጎ ተወለደ

2. በ፮ኛው ወር ገብርኤል መልአክ ከእግዚአብሄር አብ ዘንድ ተላከ ከአንዲት አገር ናዝሬት ገሊላ ከምትባልለዮሴፍ እጮኛ ከሆነች ከድንግል ዘንድ የዚች የድንግል ስሟ ማርያም ነው። መልአክ ወደ እርስዋ ገብቶ እንዲህ አላት ደስታ ይገባሻል እግዚአብሄር ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ነስቶ ከአንቺ ሰው ሆኗልና ከሴቶች ይልቅ አንቺ ቡርክት ነሽ ከቃሉ አነጋገር አይታ ደነገጠች እንዲህም አለች እንዲህ ያለ የምስጋና እጅ መንሻ ይደረግልኛል? መልአክ እንዲህ አላት ማርያም ሆይ አትፍሪ ከእግዚአብሄር ዘንድ ባለሟልነትን አግኝተሻልና እነሆ ትፀንሻለሽ ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ እርሱም ታላቅ የእግዚአብሄር ልጅ ይባላል እግዚአብሄር አምላክም የዳዊት የአባቱን ዙፋን ይሰጠዋል እርሱም ለያዕቆብ ወገን ለዘለዓለሙ ይነግሣል መንግሥቱም አያልፍም ማርያም መልአኩን እንዲህ አለችው ይህ ነገር እንደምን ይሆንልኛል? እንዘ ኢየአምር ብእሴ መልአኩም እንዲህ አላት መንፈስ ቅዱስ ይጠብቅሻል የልዑል ኃይልም ያድርብሻል ይህ የሚወ ለደውም ከሦስቱ ቅዱስ አንዱ ቅዱስ ነው እነሆ ኤልሳቤጥ ከአንቺ ወገን የምትሆን ከሽመገለች ከአረጀች በኋላ ፀነሰች ልጅም አገኘች እነሆ ይህ ስድስት ወር ሆነ መካን ሲሏት ለእግ ዚአብሄር የሚሳነው ነገር የለምና ማርያምም መልአኩን እንደ ቃልህ ይደረግልኝ እነሆ እኔ ለእግዚአብሄር ባሪያው ነኝ አለችው።

3. መልአኩ ገብርኤል ማርያም ድንግል ለአንች ክብር ምስጋና ይገባሻል አላት ምስጋና ይገባሻል ወላዲተ አምላክ ምስጋና ይገባሻል ቅድስት ነሽና ምስጋና ይገባሻል የመለኮት ማደሪያ ነሽና ምስጋና ይገባሻል የተሸለመች ድንኳን ነሽና ምስጋና ይገባሻል የመላእክት እኅት የሕዝቡ ሁሉ እናት ነሽና ምስጋና ይገባሻል የሁሉ እመቤት ማርያም ምስጋና ይገባሻል የሁሉ ፍቅረኛ ማርያም ምስጋና ይገባሻል ልዑል ማደሪያው ትሆኝ ዘንድ መርጦሻልና ምስጋና ይገባሻል በወርቅ የተሸለ ምሽ የርግብ ክንፍ በብር ያጌጥሽ ምስጋና ይገባሻል ጎኖችሽ በወርቅ አመልማሎ የተሸለሙ ለአንች ምስጋና ይገባሻል የምሥራቅ ደጃፍ የብርሃን እናቱ ለአንች ምስጋና ይገባሻል ከፀሐይ ሰባት እጅ የምታበሪ ክብርሽ ከአድባራቱ ሁሉ ከፍ ከፍ ያለ ለአንች ምስጋና ይገባሻል ማርያም ሆይ ከተመረጡ የተመረጥሽ ከተከበሩ የተከበርሽ ለአንች ምስጋና ይገባሻል ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ለምኝልን ያድነን ዘንድ በአባቱ ምስጋና ከቅዱሳን መላእክቶቹ ጋር በመጣ ጊዜ ጻድቃንን በቀኙ ኃጥ አንን በግራው ባቆመ ጊዜ እኛን ከሰማ ዕቱ እስጢፋኖስ ከመጥምቁ ዮሐንስና ከሁሉ ቅዱሳን ከሰማ ዕታትም ጋር ያቆመን ዘንድ ለምኝልን ለዓለመ ዓለም አሜን ለዘለዓለሙ ይቅር ይበለን።

ወእሙ ለብርሃን ሰላም ለኪ ትበርሂ እምፀሐይ ወትትሌዐሊ እምአድባር ሰላም ለኪ ማርያም ኅሪት ወክብርት ሰላም ለኪ።

ሰአሊ ለነ ኀበ እግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ ያድኅነነ አመ ይመጽእ በስብሐተ አቡሁ ምስለ መላእክቲሁ ቅዱሳን አመ ያቀውም አባግዐ በየማኑ ወአጣሌ በጸጋሙ ያቁመነ በየማኑ ምስለ እስጢፋኖስ ሰማዕት ወዮሐንስ መጥምቅ ወምስለ ኲሎሙ ቅዱሳን ወሰማዕት ለዓለመ ዓለም አሜን።

ጸሎታ ለማርያም ወስእለታ……